# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ማክሰኞ 84ኛ ዓመት ቁጥር 042 ጥቅምት 12 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!










# ከአፍሪካ ቀንድ ጀርባ የሚሸረቡ ሴራዎች

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

**ዜና ትንታኔ**

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግብፅ በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ እያደረገች ያለችው እንቅስቃሴ አዲስ የችግር አረንቋ የሚወልድ ስለመሆኑ ለመገመት አያዳግትም። በተለይ ኢትዮጵያ ከሶማሌ ላንድ ጋር ያደረገችውን የባህር በር ስምምነት ተከትሎ ሶማሊያ በኢትዮጵያ ላይ ተደጋጋሚ ክስ ማቅረቧን ተከትሎ ግብጽ የሶማሊያ ወዳጅ በመምሰል ነገሩን ለማባባስ ሌት ተቀን መሥራት ላይ ትገኛለች።

በነሐሴ ወር 2016 ዓ.ም. ግብፅ ከሶማሊያ ጋር ያደረገችው የጦር ስምምነት ሳያንስ ሁለተኛውን የሶስትዮሽ ስምምነት ከሶማሊያና ኤርትራ ጋር በቅርቡ መስርታለች። ይህ አካሄድ መብት ቢሆንም ከዚህ በስተጀርባ ያለው ፍላጎት ግን ሌላ ስለመሆኑ ጸሃይ የቀሞቀው ሀቅ ነው። በተለይም የግብፅ ድጋፍ ወታደራዊ ትብብር ወይስ ሕገ-ወጥ የመሣሪያ ዝውውር የሚለው

ከአፍሪካ ቀንድ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ኢትዮጵያ የምታካሂዳቸው ጉባዔዎች የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰትን እያሳደጉ ነው

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ በሀገርና ከሀገር ውጭ የምታካሂዳቸው የቢዝነስና የኢንቨስትመንት ጉባዔዎች የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰትን እያሳደጉ መሆኑን የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ከኦስትሪያ ኤምባሲ ጋር በመተባበር የኢትዮ- ኦስትሪያ ቢዝነስ ጉባዔን ዛሬ በአዲስ አበባ ያካሂዳል። ጉባዔውን አስመልክቶ በትናንትናው ዕለት በኮሚሽኑ የኢንዱስትሪ ፓርኮች እና ፕሮሞሽን ዘርፍ ምክትል ኮሚሽነር ዘለቀ ተመስገን (ዶ/ር) እና በኢትዮጵያ የኦስትሪያ አምባሳደር ሲሞን ኬናፕ (ዶ/ር) በጋራ መግለጫ ሰጥተዋል።

በኮሚሽኑ የኢንዱስትሪ ፓርኮች እና ፕሮሞሽን ዘርፍ ምክትል ኮሚሽነር ዘለቀ (ዶ/ር) ተመስገን እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ ከባለፈው ዓመት ጀምሮ ከሌሎች ሀገራት ጋር በመሆን የቢዝነስና ኢንቨስትመንት ጉባዔዎችን እያዘጋጀች ነው። በ2016 ዓ.ም ከፓኪስታን፣ ሩሲያ፣ ሳዑዲ፣ ቻይናና ከሌሎች የተለያዩ ሀገራት ጋር በአዲስ አበባና ከኢትዮጵያ ውጭ

ኢትዮጵያ የምታካሂዳቸው ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ተሻለ በሬቻ(ዶ/ር)

## ዘንድሮ ከግማሽ ሚሊዮን በላይ ተማሪዎች የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና እንደሚቀላቀሉ ይጠበቃል

ገጽ 3

# የትምህርት ቤት ምገባ- ከነዋሪዎች እፎይታ እስከ ትውልድ ግንባታ

**አዲሱ ገረመው**

በአዲስ አበባ ከተማ በዘንድሮው ዓመት ከ801 ሺህ በላይ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ምገባ ተጠቃሚ መሆናቸውን ሰሞኑን በመዲናዋ በተካሄደው የሚላን የከተሞች ምገባ ስምምነት ፎረም ላይ ተጠቅሷል። የትምህርት ቤት ምገባው ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስካሁን ባሉ ሂደቶች ለሀገሪቱ ዜጎች ብሎም ለተማሪዎች ምን ፋይዳ ይዞ መጣ?

እ.ኤ.አ.በ2021 የተባበሩት መንግሥታት የዓለም ምግብ ፕሮግራም ሪፖርት እንደሚያመለክተው የትምህርት ቤት ምገባ አስፈላጊ የሆነ የተመጣጠነ ምግብ በማቅረብ በተለይም ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው አካባቢዎች የትምህርት ክንዋኔን የሚያሳድግ ነው።

እንደ ብራዚል እና ህንድ ያሉ ሀገራት መጠነ ሰፊ

የትምህርት ቤት ምገባ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






# በአዲስ አበባ ከተማ የዳቦ ስርጭትና አቅርቦትን ለማስፋት በርካታ ጥረቶች እየተደረጉ ነው

**ቃልኪዳን አሳዬ**



አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ የዳቦ ስርጭትና አቅርቦትን ለማስፋት በርካታ ጥረቶች እየተደረጉ መሆኑን የከተማው ንግድ ቢሮ አስታወቀ።

የቢሮው የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር ሰውነት አየለ ለኢፕድ እንደተናገሩት፤ በአዲስ አበባ ከተማ የዳቦ ስርጭትና አቅርቦትን ለማስፋት የከተማ አስተዳደሩ ንግድ ቢሮ ከአቅርቦት ጋር በተያያዘ በሶስት መንገዶች እየሠራ ይገኛል።

በዚህም በከተማዋ በሚገኙ የሸገር ዳቦ የማከፋፈያ ሱቆች፣ በከተማ አስተዳደሩና በባለሀብቶች ጥምረት በተገነቡ 20 የዳቦ ፋብሪካዎች፤ እንዲሁም ከ1 ሺህ 300 በላይ በሆኑ በግል ዳቦ ቤቶች አማካኝነት ዳቦ ለህብረተሰቡ እንዲሰራጭ እየተደረገ ነው ብለዋል።

ከዚህ አኳያ ቢሮው ባለፉት ሶስት ወራት ውስጥ በሸገር ዳቦ፣ በግል ባለሀብቶችና በመንግሥት አጋርነት በተገነቡ ዳቦ ቤቶች አማካኝነት ከ86 ሚሊዮን በላይ ዳቦዎችን ለህብረተሰቡ እንዲሰራጭ መደረጉን ያነሱት ዳይሬክተሩ፤ ከተማ አስተዳደሩ ድጎማ የሚያደርግባቸው የሸገር ዳቦዎች 70 ግራም እንደሆኑና በአምስት ብር እየተሰራጩ እንደሚገኝ ጠቁመዋል።

እንደ አቶ ሰውነት ገለጻ፤ የመንግስትና የግል ባለሀብቶች በተገነቡ የዳቦ ፋብሪካዎችና በግል ዳቦ ቤቶች አማካኝነት ተመጣጣኝ በሆነ ዋጋ ዳቦ ለህብረተሰቡ ተደራሽ እንዲሆን ቁጥጥር እየተደረገ ይገኛል። በዚህም የህብረተሰቡን የዳቦ ፍላጎት ለማሟላት በሸገር ዳቦና በሌሎች አማራጮች በመጠቀም ጥረት እየተደረገ ነው።

በተለይም የሸገር ዳቦዎች አነስተኛ ገቢ ባላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ተመራጭ መሆናቸውን የገለጹት አቶ ሰውነት፤ በአሁኑ ወቅትም በቀን ከ500 ሺህ እስከ 550 ሺህ ዳቦዎች ተጋግረው ከነዋሪዎች በተጨማሪ ለምገባ ማዕከላትና ለበጎ ፍቃድ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች እየተሰራጩ መሆኑን ተናግረዋል።

ዳይሬክተሩ አክለውም፤ እነኚህ ዳቦዎችም በሁሉም ክፍለ ከተሞች በሚገኙ ከ430 በላይ የሸገር ዳቦ መሸጫ ሼዶች አማካኝነት ጠዋትና ማታ ለህብረተሰቡ እየቀረቡ ይገኛል ነው ያሉት።

በአሁኑ ወቅት አብዛኞቹ የሸገር ዳቦ መሸጫ ሼዶች አገልግሎት እየሰጡ ሲሆን ከልማት ጋር በተያያዘ እየተነሱ ያሉም ከሆነ እየተጠና አማራጭ ቦታዎችን በማፈላለግ መልሰው የሚደራጁበት ሁኔታ እንደሚኖር ያመላከቱት አቶ ሰውነት፤ የስርጭት መጠኑንና አቅርቦቱን ለማስፋት የሸገር ዳቦን ከሚያመርተው ኩባንያ እና ምርቱን ተቀብለው ከሚያሰራጩ ወጣቶች ጋር የጋራ መድረኮችን በማዘጋጀት ችግሮች እንዲቀረፉ እንደሚደረግ ገልጸዋል።

በከተማዋ በሶስቱም አማራጮች በሚቀርቡ ዳቦዎች ላይ ከአቅርቦት፣ ከጥራትና ግራም ጋር በተያያዘ ሰፊ ቁጥጥሮች እየተደረጉ ነው። ለዚህም ዜጎች በከተማዋ በተለያዩ አማራጮች በቂ የዳቦ አቅርቦት በመኖሩ ገዝተው መጠቀም እንደሚችሉ ዳይሬክተሩ ጠቁመዋል።

# በወላይታ ዞን የወባ ወረርሽኝ እንዳይከሰት የመከላከል ሥራ እየተሠራ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ወላይታ፡- የወላይታ ዞን የወባ በሽታ መከላከል ግብረ ኃይል ወባን ለመከላል የተለያዩ የቅድመ ጥንቃቄ ሥራዎችን እየሠራ መሆኑን አስታወቀ፡፡ ጥቅምት 5 ቀን 2017 ዓ.ም. በበሽታው አስከፊነትና መቆጣጠሪያ ስልቶች ዙሪያ በሶዶ ከተማ ምክክር አድርጓል፡፡

በሶዶ ከተማ በተደረገው ምክክር ላይ ንግግር ያደረጉት የግብረ ኃይሉና የወላይታ ዞን ዋና አስተዳዳሪ ተወካይ አቶ ታምራት በለጠ በዞኑ እየተባባሰ የመጣውን የወባ ስርጭት በጤና ባለሙያዎች፣ በአመራር አካላት፣ በሕዝብና በባለድርሻዎች ተሳትፎ ለመከላከልና ለመቆጣጠር እንደሚቻል ጠቁመዋል።

በሽታውን ካልተቆጣጠርን የከፋ መዘዝ ሊያስከትል ይችላል ያሉት ተወካዩ የሕዝቡን ሕይወት ለመታደግ በቁርጠኝነትና በተጠያቂነት መንፈስ መሥራት የሁላችንም ኃላፊነት ነው ብለዋል።

የዞኑ ወባ መከላከል ግብረ ኃይል ፀሀፊና የጤና መምሪያ ኃላፊ አቶ ፀጋዬ ኤካ በበኩላቸው እየተባባሰ የሚገኘውን የአየር ንብረት ለውጥ ተከትሎ በዞኑ እየጨመረ የመጣውን የወባ ስርጭት የመከላከልና የመቆጣጠር ሥራዎች ግብረ ኃይሉ በትኩረት እንደሚመራ አንስተዋል።

ከህክምና አንፃር የመከላከሉ ሥራ ወጪው እምብዛም መሆኑን ተናግረው በቅድሚያ የወባ ትንኝ መራቢያ ሥፍራዎችን የማፋሰስ እና የማዳፈን ሥራን ጨምሮ የአጎበር አጠቃቀም ማጎልበት በእጅጉ ይመከራል ብለዋል።

የታመመውን ሰው ሙያዊ ሥነ-ምግባር በተላበሰ መልኩ ማከም ሠብዓዊና ሞራላዊ ግዴታ መሆኑን ገልፀው ታካሚዎች ደግሞ ኃላፊነት ከሚሰማው የጤና ተቋም በባለሙያ የታዘዘውን መድኃኒት በአግባቡ እንዲጠቀሙ አቶ ፀጋዬ አስገንዝበዋል።

በመምሪያው በሽታ የመከላከልና ጤና የማጎልበት ዳይሬክቶሬት ቡድን መሪ አቶ አንበሳው ወልዴ ለውይይት ባቀረቡት ጥናታዊ ሰነድ በዞኑ ባለፉት አምስት ዓመታት የወባ ስርጭት እየጨመረ መምጣቱን አመላክተው በ2016 ዓ.ም መጨረሻ አካባቢ የበሽታው ታካሚዎች ቁጥር ከአንድ መቶ ሺህ በላይ መድረሱን ገልፀዋል።



**አቶ ፀጋዬ ኤካ**

ስርጭቱን ለመግታት የሚያስችል የተቀናጀና ተመጣጣኝ ጥረት ማድረግ ከጤና ባለሙያዎች፣ ከአመራር አካላት፣ ከህብረተሰቡና አጋር ድርጅቶች እንደሚጠበቅም አመላክተዋል።

የአረካ ከተማና የቦሎሶ ቦምቤ ወረዳ ጤና ጥበቃ ጽህፈት ቤት ኃላፊዎች በበኩላቸው በሰጡት አስተያየት የአካባቢ ቁጥጥር ከማሳለጥ በተጓዳኝ በአጎበር አጠቃቀም ላይ የሚስተዋሉ ውስንነቶችን ለማረም አቅደው እየሠሩ እንደሚገኙ ገልጸዋል።

ፈዋሽነቱ ባልተረጋገጠ ሕገ ወጥ የመድኃኒት ዝውውር በሚያከናውኑትና ሙያዊ ሥነ ምግባርን በሚጥሱ ስግብግቦች ላይ ሕጋዊ እርምት እየተወሰደ እንደሚገኝም አመላክተዋል።

# በሩብ ዓመቱ 93 ሺህ ዩኒት ደም ተሰብስቧል

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- በ2017 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት 93 ሺህ ዩኒት የሚደርስ ደም መሰብሰብ መቻሉን የኢትዮጵያ የደምና ሕብረ ሕዋስ ባንክ አገልግሎት አስታወቀ።

የአገልግሎቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ሀብታሙ ታዬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በ2017 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት 100 ሺህ ዩኒት ደም ለመሰብሰብ ታቅዶ 93 ሺህ ዩኒት የሚደርስ ደም መሰብሰብ ተችሏል። አፈጻጸሙም ከ90 በመቶ በላይ ይሆናል።

አፈጻጸሙ ከደም ባንክ ደም ባንክ እንዲሁም ከክልል ክልል ይለያያል ያሉት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፤ ከዚህ ውስጥ 28 ሺህ ዩኒት ደም አዲስ አበባ ውስጥ የተሰበሰበ ነው። አዲስ አበባ፣ ጅግጅጋ፣ ኦሮሚያ አብዛኛው አካባቢ ያሉ ደም ባንኮች ጥሩ ውጤት ያስመዘገቡ ናቸው።

ጥሩ እቅስቃሴ ያሳዩ ደም ባንኮች የበለጠ እዲሠሩ በተወሰነ ምል ዝቅ ያለ አፈጻጸም ያስመዘገቡትንም ወደተሻለ ደረጃ ለማምጣ ሥራዎች እንደሚሠሩ ጠቅሰዋል።

ትምህርት ቤቶች መከፈታቸው ተከትሎ በትምህርት ቤቶች የደም መሰብስብ ሥራ እየተሠራ ነው። በዚህም የተሻለ ውጤት መገኘት መጀመሩን አስታውቀዋል።

ከዓመት ዓመት የማህበረሰቡ ደም የመለገስ ግንዛቤ እየተሻሻለ ነው ያሉት አቶ ሀብታሙ፤ ያለው ሀገራዊ የደም ፍላጎትም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ነው።

በዓለም ጤና ድርጅት መስፈርት መሠረት የአንድ ሀገር የደም ፍላጎት ተሟላ ተብሎ የሚወሰደው ቢያንስ አንድ በመቶ የሚሆነው ሕዝብ ደም ሲለግስ ነው።

ከዚህ አንጻር ስናየው ባለፈው ዓመት እንደሀገር የተሰበሰበው 350 ሺህ ዩኒት ደም ነው። ይህም የአጠቃላይ ሕዝቡን ዜሮ ነጥብ 3 በመቶ ብቻ ነው።

አጠቃላይ ባህል ሆኖ ሰዎች መጥተው ደም እየለገሱ የሕክምና ተቋማት ፍላጎት የማሟላት ሁኔታ ገና ብዙ መሥራት እንዳለብን የሚያመላክት ነው ብለዋል።



**አቶ ሀብታሙ ታዬ**

የማህረሰቡን ግንዛቤ ለማሳደግም መገናኛ ብዙሃንን ጨምሮ ሌሎችም ባለድርሻ አካላትን ትብብር የሚፈልግ በመሆኑ ሁሉም የየድርሻቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱም ጠቀይቀዋል።

አብዛኛው ደም በትምህርት ቤቶች እንደሚሰበሰብ ጠቅሰው፤ ይህን ሥራ ለማጠናከር በቅርቡ 450 ከሚሆኑ የትምህርት ቤት ዳይሬክተሮች ጋር ምክክር ተደርጓል። ለተማሪዎች ግንዛቤ ለመፍጠርም ሥራዎች ይሠራሉ። ከእምነት ተቋማት፣ ከደም ልገሳ ማህበራትና ከሌሎችም ባለድርሻዎች ጋርም በትብብር ይሠራል ብለዋል።

ደም በማጣት ሕይወታቸውን እስከ ማጣት የሚደርሱ ሰዎች አሉ ያሉት አቶ ሀብታሙ፤ ከ18 እስከ 65 እድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ፣ በደም ከሚተላለፉ በሽታዎች ነጻ የሆነና ክብደቱ ከ45 ኪሎ በላይ የሆነ ማንኛውም ሰው ደም በመለገስ የሕይወት አድን ሥራ ላይ እንዲሳተፍ ጥሪ አቅርበዋል።

## ኮሚሽኑ ከፍተኛ አመራሩ ላይ ትኩረት ያደረገ የሀብት ምዝገባ እያካሄደ ነው

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- የሀብት ምዝገባ ውሳኔ የሚያሳልፉ አካላት ሥራዎቻቸውን በሚተገብሩበት አጋጣሚ ሃላፊነታቸውን ከግል ጥቅማቸው ጋር እንዳያቀላቅሉ እና ግልጽነትና ተጠያቂነትን በማስፈን ሂደት ሁነኛ መሣሪያ መሆኑን የፌዴራል ሥነምግባርና ጸረ ሙስና ኮሚሽን ገለጸ።

በኮሚሽኑ የሙስና መረጃዎች አስተዳደር መሪ ሥራ አስፈጻሚ መስፍን በላይነህ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የሀብት ምዝገባና ማሳወቅ ሥር ካሉ የተለያዩ አሠራሮች መካከል አንዱ የግልጽነት ማስፈኛ መሣሪያ ነው።

የሀብት ምዝገባው የሚከናወነው ትኩረት በሚሹ ጉዳዩች ላይ ሲሆን ዋና ትኩረቱም ሙስናና ብልሹ አሠራርን መከላከል ነው። ትኩረቱን በመንግሥት መስሪያ ቤቶች፣ በመንግሥት የልማት ድርጅቶችና በሕዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ አድርጎ እንደሚተገበርም ተናግረዋል።

በአብዛኛው በኢትዮጵያ ሙስናና ብልሹ አሠራሮች ከአገልግሎት አሰጣጥ ጋር ስለሚያያዝ በተለይም ውሳኔ ከሚያሳልፉ የበላይ ሃላፊና አመራር ጋር እንደሚገናኝ ጠቁመዋል።

የሀብት ምዝገባ በትኩረት በተለዩ የሥራ መደቦችና ዘርፎች ላይ ሲያተኩር የተሻለ ውጤት እንደሚያመጣ እንደሚጠበቅም ጠቁመዋል። ከከፍተኛ አመራሩ እስከ ቡድን መሪ የሚተላለፉ ውሳኔዎች በመንግሥትና በሕዝብ ሀብት ላይ ትልቅ አሉታዊ ተጽእኖም አወንታዊ ፋይዳም አለው ብለዋል።

በአዋጁ ከተቀመጡ አራት የምዝገባ አይነቶች ኮሚሽኑ ትኩረት ያደረገው ዘርፍ ተኮር የሀብት ምዝገባ ሥርዓት ላይ ሲሆን፤ ሥርዓቱ ከከፍተኛ አመራሩ እስከታችኛው በየደረጃው ያለውን አመራር እንደሚያካትትም አመልክተዋል። ትግበራው ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤት እስከታችኛው አካል እንደሚያካትት እንዲሁም ተሿሚውን፣ የሥራ ሃላፊውን እና እስከ ቡድን መሪ እንዲያካትት ተደርጎ እየተሠራ መሆኑንም አመልክተዋል።

የሀብት ምዝገባ ህዳር ወር 2003 ዓ.ም በወረቀት ምዝገባ እንደተጀመረ የጠቆሙት አቶ መስፍን፤ የወረቀት ምዝገባ ሥራው የመረጃ ጥራትን የማያመጣና ከፍተኛ ወጪ ስለሚጠይቅ መቀየር ማስፈለጉን ተናግረዋል።

የሌሎች ሀገራት ልምድም የሀብት መመዝገቢያ መተግበሪያ ሲስተም ሰርተው ከሃርድ ኮፒ ወደ ሶፍት ኮፒ በመቀየር በቀላሉ ሀብት አስመዝጋቢዎች የሚሞሉበትን አሠራር በመተግበር ወጪን እና ጊዜን ይቆጥባሉ፣ የመረጃ ጥራትንም ይጨምራሉ ብለዋል።

ወደ ሲስተም ለማስገባት አቅጣጫ ተቀምጦ እየተሠራ መሆኑን በመጠቆም፤ ለጊዜው መለስተኛ መተግበሪያዎችን በመጠቀም በሶፍት ኮፒ እየተሞላ መሆኑን ጠቅሰዋል።

ኮሚሽኑ ይህንን በመገንዘብ ሲስተሙን ወቅታዊ ለማድረግ እየሠራ መሆኑን የጠቆሙት አቶ መስፍን፣ አንድ ሀብት አስመዝጋቢ እንደተሾመ፣ እንደተቀጠረ ወይም እንደተመደበ በ45 ቀናት ውስጥ ሀብት ማስመዝገብ እንዳለበት፣ ሁለት ዓመት ሲሞላውም እድሳት ማድረግ እንዳለበት አዋጁ እንደሚደነግግም አመልክተዋል።

አቶ መስፍን እንዳሉት፤ ኮሚሽኑ አሁን ባለው ነባራዊ ሂደት ሥልጣኑ የሥነምግባር ግንባታ እና የሙስና መከላከል ተግባሮችን ማከናወን ነው። በበይነ መረብ በመጠቀም ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ እየተሠራ ቢሆንም የበጀት ጉዳይ አሳሳቢ ነው።

“የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች ከዚህ በፊት ተጠሪነታቸው ለኮሚሽኑ ነበር። አሁን ተጠሪነታቸው ለየተቋማቱ ነው። በተለይ የሥነምግባርና የሙስና መከላከል ሥራዎች ላይ የተወሰነ ጫና ያሳድራል። ተጠሪነታቸው ለተቋማቱ መሆኑ ለሥራው ምቹ አይደለም” ብለዋል።

የሥነምግባርና ሙስና መከላከል ጥናቶች ከተካሄዱ በኋላ የሚለዩ ችግሮቹን መሠረት በማድረግ በሚሰጡ ምክረ ሃሳቦች በአንዳንድ ተቋማት ላይ ችግሮቹን ተጨባጭ በማድረግ እና በባለቤትነት በመያዝ መፍትሄ መስጠት ላይ ክፍተት አለ ሲሉም አስረድተዋል።

ሁሉም ክልሎች እንዲሁም ሁለቱም ከተማ መስተዳድሮች የሥነምግባርና ጸረ ሙስና ኮሚሽን አላቸው። ይብዛም ይነስም በየሩብ ዓመቱ በትስስር ጉባዔ ሥራዎች መገምገማቸውን በጥንካሬ አንስተዋል።

ኮሚሽኑም ሥራዎችን በሲስተም እንዲሠሩ በማድረግ የማቅለልና ለሙስና ጠቋሚዎች እና ለሀብት አስመዝጋቢዎች ምቹ የማድረግ ጥሩ ጅምር ተግባራት በበጎነት እንደሚጠቀሱም አመልክተዋል።

## ዘንድሮ ከግማሽ ሚሊዮን በላይ ተማሪዎች የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና እንደሚቀላቀሉ ይጠበቃል

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- በዘንድሮ የትምህርት ዘመን ከ 526 ሺ. በላይ ተማሪዎች የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ይቀላቀላሉ ተብሎ እንደሚጠበቅ የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር የ2017 የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና የመግቢያ መቁረጫ ነጥብን በትናንትናው እለት አሳውቋል።

በሥራና ክህሎት ሚኒስቴር የቴክኒክና ሙያ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ተሻለ በሬቻ(ዶ/ር) እንደገለጹት ፤ የመቁረጫ ነጥቡ በ2016 ዓ.ም የ12ኛ ክፍል ማጠናቀቂያ ፈተና የወሰዱ ተማሪዎችን ታሳቢ ተደርጎ የተሰላ ሲሆን የሚያገለግለውም ለ2017 የሥልጠና ዘመን ብቻ ነው፡፡

በዚህም መሠረት በደረጃ አንድና ሁለት የሚመዘገቡ ሰልጣኞች በአስራ ሁለተኛ ብሄራዊ ፈተና ወንዶች 141 እና ከዚያ በታች፣ ሴቶች 138 እና ከዚያ በታች ያመጡ ናቸው።

ለታዳጊ ክልሎችና አርብቶ አደር አካባቢዎች ለወንዶች 137ና ከዚያ በታች፣ ለሴቶች 134ና ከዚያ በታች፣ ለሁሉም ክልል አካል ጉዳተኞች 124ና ከዚያ በታች ያመጡ መሆኑንም ገልጸዋል።

በደረጃ ሶስትና አራት የሚመዘገቡ በ12ኛ መልቀቂያ ፈተና ወንዶች 142ና ከዚያ በላይ፣ ሴቶች 139ና ከዚያ በላይ ያመጡ መሆናቸውን አስታውቀዋል።

ለታዳጊ ክልሎችና ከአርብቶ አደር አካባቢዎች ለወንዶች 138 እናና ከዚያ በላይ፣ ለሴቶች 135ና ከዚያ በላይ፣ ለሁሉም ክልል አካል ጉዳተኞች 125ና ከዚያ በላይ ያስመዘገቡ ናቸው።

በደረጃ አምስት የሚሰለጥኑ ወንዶች 179ና ከዚያ በላይ፣ ሴቶች 170ና ከዚያ በላይ ያስመዘገቡ ተማሪዎች ሥልጠናውን ለመውሰድ መስፈርቱን የሚያሟሉ ሲሆን ከታዳጊ ክልሎችና ከአርብቶ አደር አካባቢዎች ወንዶች 167ና ከዚያ በላይ፣ ሴቶች 162ና ከዚያ በላይ እንዲሁም ከሁሉም ክልል አካል ጉዳተኞች 154ና ከዚያ በላይ ያስመዘገቡት በደረጃ አምስት ገበተው መሠልጠን እንደሚችሉ ሚኒስትር ዴኤታው አብራርተዋል።

ሚኒስትር ዴኤታው በተለያዩ የሥልጠና አይነት ወደ ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ሊገቡ የሚችሉት ሠልጣኞች ብዛት 526 ሺ683 ይሆናሉ ተብሎ እንደሚጠበቅ የገለጹ ሲሆን ከባለፉት ዓመታት ልምዶች በመነሳት በመደበኛ ሥልጠና ተመዝግበው ይሰለጥናሉ ተብለው ከሚጠበቁት ሠልጣኞች መካከልም 30 በመቶ የሚሆኑት በአጫጭር የሥልጠና ፕሮግራም ሊሰለጥኑ እንደሚችሉ ታሳቢ


ተሻለ በሬቻ(ዶ/ር)

መደረጉን አብራርተዋል፡፡

ዶ/ር ተሻለ ከ2016 የትምህርት ዘመን በፊት የ12ኛ ክፍል ማጠናቀቂያ ፈተና የወሰዱ ተማሪዎች በዚህ የሥልጠና ዘመን ወደ ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ገብተው መሰልጠን ቢፈልጉ በየሥልጠና ዘመኑ በነበረው የመቁረጫ ነጥብ መስፈርት መሠረት የሚስተናገዱ መሆኑ ገልጸዋል፡፡

## የኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ በሚቀጥለው ወር ሥራውን ይጀምራል

### - 400 ሺህ የሚደርሱ ኢትዮጵያውያን አክሲዮን አላቸው

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ በሚቀጥለው ወር ሥራውን ለመጀመር እየሠራ መሆኑን ገለጸ። 400 ሺህ የሚደርሱ ኢትዮጵያውያን አክሲዮን እንዳላቸውም ተገልጿል።

የኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ሥራ አስፈጻሚ ጥላሁን እስማኤል (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ወደ ሥራ ለመግባት የሚያስችሉት አብዛኞቹን የዝግጅት ሥራዎች በመጠናቀቃቸው ሌሎች ነገሮች ካላስቆዩ በቀር በሚቀጥለው ወር በይፋ ይጀመራል።

የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያው አስፈላጊ ግብዓቶች ግዢ መፈጸሙንና ቴክኖሎጂው ሙከራ ላይ እንደሚገኝ የገለጹት ሥራ አስፈጻሚው፣ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለማገበያየት አገናኝ አባላት /ደላሎች/ ያስፈልጋሉ ብለዋል።

አገናኝ አባላት በካፒታል ገበያ ባለሥልጣን ፍቃድ አግኝተው ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ አባል መሆን እንዳለባቸው በመግለጽ፣ ስለዚህ አንድም ሁለትም አገናኝ አባላት እንደተገኘ ገበያውን በይፋ ማስጀመር እንደሚቻል



ጥላሁን እስማኤል (ዶ/ር)

ተናግረዋል።

ገበያው አክሲዮናቸው መሸጫ መለወጫ መድረክ መሆኑን ጠቅሰው፣ የአክሲዮን ዋጋን በማቅረብ በሰከንዶች ውስጥ ከየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል፣ ውጪውንም ጨምሮ መግዛትና መሸጥ እንዲችሉ መድረክ ሆኖ እንደሚያገለግል አስረድተዋል።

የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያው ግብ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ከየትም ቦታ ሆኖ ባለው አቅም እንዲቆጥብበት ማድረግ ነው ያሉት ጥላሁን (ዶ/ር)፣ አክሲዮን ወደ ፊት ለልጆች ማስተማሪያ አድርጎ ለመሸጥ፣ ውርስ ለማድረግ መቆጠቢያ መንገድ ነው ብለዋል።

ጥላሁን (ዶ/ር) አክለውም፣ ወደ ፊት አክሲዮኖች ኤሌክትሮኒክ እንደሚሆኑ ጠቅሰው፣ ዜጎች መገበያየት ሲፈልጉ በአገናኝ አባል በኩል፣ ከሞባይል አፐሊኬሽን ላይ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ መግዛትና መሸጥ እንደሚችሉ ገልጸዋል።

በሰነድ ሙዓለ ነዋዮች ገበያ አባል ለመሆን የአባልነት ምዝገባና ሰርተፍኬት እንደሚያስፈልግ በመግለጽ፣ ለኢንቨስተሮች የውስጥ ደንቦችን በማስተማርና በመፈተን ሥልጠናዎችንም በመስጠት አስፈላጊውን መስፈርት ሲያሟሉ የአገበያይነት ፈቃድ እንደሚሰጥም ጠቁመዋል።

በአሁኑ ወቅት 400 ሺህ የሚደርሱ ኢትዮጵያውያን የባንኮችንና ኢንሹራንስ ኩባንያዎችን አክሲዮን መግዛታቸውን ጠቅሰው፣ ከአሁን ቀደም አክስዮን መሸጥ ለሚፈልግ ሰው የሚያገለግል ማዕከላዊ ገበያ እንዳልነበር ተናግረዋል።

ይህንንም ተከትሎ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ፈቃድ መስጠት የሚያስችል መመሪያ በካፒታል ገበያ ባለሥልጣን ወደ ትግበራ እንዲገባ መደረጉን ጠቁመዋል።

## ኮሚሽኑ በበጀት ዓመቱ 8 ቢሊዮን ብር ካፒታል ለማስመዝገብ አቅዷል

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- በበጀት ዓመቱ 8 ቢሊዮን ብር ካፒታል ለማስመዝገብ ማቀዱን የአዲስ አበባ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን አስታወቀ።

የአዲስ አበባ ኢቨስትመንት ኮሚሽን ዕቅድና በጀት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ወ/ሮ እናትነሽ ታመነ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጀት እንደገለጹት፤ ኮሚሽኑ በ2017 የሥራ ዘመን በአገልግሎት እና በማምረቻ ዘርፍ ስምንት ቢሊዮን ብር ካፒታል ለማስመዝገብ አቅዷል።

ከተማዋ ላይ ያለው የኢንቨስትመንት ሥራ በአራት ሥራ መስኮች ላይ ያተኮረ ነው ያሉት ወ/ሮ እናትነሽ እነሱም ማኑፋክቸሪንግ ፣ አገልግሎት ፣ የከተማ ግብርና እና ኮንስትራክሽን ናቸው ብለዋል።

የሚሰበሰበውን የገቢ ዕቅድ ለማሳካት በዋናነት ለባለሀብቱ ፈጣን እና ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት፣ ባለሀብቱ ባለበት ሆኖ ስለ ኢንቨስትመንት መረጃ እንዲኖረው በማድረግ ፣ የኦንላይን አገልግሎት እንዲሰጥ በማድረጉ እንዲሁም ለአገልግሎት ክፍያዎችን በካሽ እና ከፖስት ማሽን በተጨማሪ በቴሌ ብር እና በሲቢኢ ብር እንዲጠቀሙ የማድረግ ሥራ በትኩረት ይሠራል ሲሉ ገልጸዋል።


የሥራ እድል ፈጠራን በተመለከተ ፕሮጀክቶችን ወርዶ በመደገፍ እና በመከታተል ወደ ሥራ እንዲገቡ በማድረግ የተሻለ የሥራ ዕድል እንዲፈጥሩ ለማድረግ እየተሠራ ሲሆን በቴክኖሎጂው ረገድ ደግሞ ተቋሙ የሚሰጣቸው አገልግሎቶች አብዛኛው በቴክኖሎጂ በመደገፍ የሚሰጡ ናቸው ብለዋል።

በዚህ በጀት ዓመት የኢንቨስትመነት ፈቃድና ፈቃድ ነክ አገልግሎቶችን ኦን ላይን ለማድረግ ዝግጅት መጠናቀቁን ገልጸው የመዝገብ ቤትን ዲጂታላይዝ የማድረግ ሥራውም ትኩረት ተሰቶት ወደ ሥራ ተገብቷል ብለዋል።

ኮሚሽኑ ባለሀብቶች የሚያነሱትን ጥያቄ ለመመለስ የተለያዩ ተግባራትን እያከናወነ ሲሆን ለአብነትም የምንዛሬ እጥረት ያለባቸውን ፍራንኮ ቫሉታ ወይም ቀረጥና ታክስ ከፍለው እንዲያስገቡ ድጋፍ እያደረገ ይገኛል ሲሉ ገልጸዋል።

ሌላው የመሥሪያ ቦታ እና ብድርን በተመለከተ ተቋሙ በራሱ የማይፈታቸውን ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመሥራት ከተቋማት ጋራ ሰነድ ተፈራርሞ ወደ ሥራ ገብቷል ብለዋል።

በተጨማሪም ባለሀብቶች የሚጠይቁትን የድጋፍ አገልግሎቶት ፈጣን እና ቀልጣፋ በሆነ መንገድ ለመስጠት እና


ወ/ሮ እናትነሽ ታመነ

በተደጋጋሚ የሚያነሷቸውን የመሬት እና የብድር ጥያቄዎችን ለመመለስ ትክለኛነቱን ለማረጋገጥ አመራሩ በትክክል መሥሪያ ቦታው ላይ በመሄድ ችግሩን የማጣራት ሥራ እየሠራና እነዚህን ችግሮችን በቀጣይነት ለመፍታት እንዲያመች ከተቋማት ጋር በቅንጅት ለመሥራት ሰነዶች አዘጋጅቶ በመፈራረም ላይ ይገኛል ብለዋል።

# የትምህርት ቤት ምገባ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የትምህርት ቤት ምገባ ፕሮግራሞችን በተሳካ ሁኔታ ተግባራዊ ካደረጉ ሀገራት ውስጥ መሆናቸውን በዓለም የምግብና ግብርና ድርጅት በኩል ይገለጻል። የብራዚል ትምህርት ቤት ምገባ ፕሮግራም ከጊዜ ወደ ጊዜ በመስፋፋት አሁን በየቀኑ በርካታ ተማሪዎችን መድረስ ችሏል። ይህም የጤና እና የትምህርት ውጤቶችን ለማሻሻል የጎላ አስተዋጽኦ አበርክቷል።

በተመሳሳይ ህንድ ለበርካታ ሚሊዮን ህጻናት ምግብ በማቅረብ ከዓለም ግንባር ቀደም ከሚባሉት ሀገራት ውስጥ ትጠቀሳለች። እኤአበ2020 የህንድ ትምህርት ሚኒስቴር እንደዘገበው፣ ፕሮግራሙ የትምህርት ቤት ምዝገባን በከፍተኛ ደረጃ ከፍ አድርጎ በልጆች ላይ ያለውን የተመጣጠነ ምግብ እጥረት ቀንሷል።

ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣው የምግብ ዋስትና እና የኢኮኖሚ ችግር የትምህርት ቤት ምገባ ፕሮግራም በአዲስ አበባ ከተማም እንዲጀመር ምክንያት መሆኑ ይገለጻል።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምገባ ኤጀንሲ ምክትል ዋና ዳይሬክተርና የምግብ ግብዓት አቅርቦት ዘርፍ ኃላፊ አቶ ምነወር ኑረዲን እንደሚገልጹት፣ አዲስ አበባ ትልቅ ከተማ ከመሆኗ የተነሳ ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር ያለባት ናት። የሕዝብ ቁጥሩ ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ የሥራ አጥ ቁጥሩም ከፍ ያለና ችግር ውስጥ ያሉ የማህበረሰብ ክፍሎች በርካቶች ናቸው።

በችግር ውስጥ ያሉ የጎዳና ተዳዳሪዎችና አረጋውያን ቁጥራቸው ከፍ ያለ ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ ደግሞ ብዙዎቹ የዕለት ጉርስ ማግኘት የማይችሉ መሆናቸውንም ጠቅሰዋል። እነዚህ ዜጎች የዕለት ጉርስ ከማግኘታቸው በተጨማሪ የትምህርት ግብዓትና ምግብ አሟልተው ልጆቻቸውን ትምህርት ቤት ልከው ለማስተማር የሚቸገሩ ናቸው ይላሉ።

በሀገሪቱ አዲስ ለውጥ መምጣቱን ተከትሎ የከተማ አስተዳደሩ ከወሰዳቸው በርካታ ሥራዎች አንዱ የትምህርት ቤት የምገባ መርሀ ግብር መጀመር መሆኑን ይናገራሉ። ለዚህም ኤጀንሲ በማቋቋም አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎችን አውጥቶ በጀት መድቦ ወደ ሥራ መግባቱን ገልጸዋል።

አቶ ምነወር እንደሚሉት፤ ሥራው ሲጀመር የተጠቃሚ ተማሪዎች 300 ሺህ የነበረ ሲሆን ዛሬ ላይ ከ801 ሺህ ባለይ ደርሷል። ከአንድ ሚሊዮን 34ሺህ በላይ ተማሪዎች የዩኒፎርምና ሌሎች የትምህርት ግብዓቶች ማቅረብ ተችሏል። ይህ በመሆኑ ወላጆች እፎይታ አግኝተዋል። ተማሪዎችም ትምህርታቸው ላይ ትኩረት በማድረግ እየተማሩ ይገኛሉ። ይህም ከትምህርት ገበታ ላይ መቅረትና መውደቅን የቀነሰ ሆኗል። የትምህርት ተሳትፎ ቁጥር እንዲጨምርም አድርጓል።

ኤጀንሲው ከነዋሪዎች እፎይታ እስከ ትውልድ ግንባታ በሚል መርህ ነዋሪዎች ላይ የሚታዩ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮችን በመቅርፍና እፎይታን በመስጠት የነገውን ሀገር ተረካቢ ዜጋ ለማፍራት በቁርጠኝነት እየሠራ መሆኑንም ነው የገለጹት።

በደጃዝማች ወንድይራድ ትምህርት ቤት የምገባ አስተባባሪ ወይዘሮ የምስራች ሙኩሪያ እንደሚሉት፤ ምገባው ህጻናት በአእምሮ፣ በአካልና መንፈስ እንዲጠነክሩ ታስቦ የሚዘጋጅ ነው። ከላይ የወረዳውን መመሪያ ተፈጻሚ ለማድረግም ጠንካራ ቁጥጥር አለ። ውጤቱም የተሻለ ነው። ሥራው ደረጃውን በጠበቀ መልኩ የሚሠራ ሲሆን የምግብ ዝርዝር የሚጓደልበት ሁኔታም አይኖርም። ለዚህ ደግሞ ከመምህራን ጭምር የተውጣጡና የምገባውን ሁኔታ የሚቆጣጠሩ አካላት አሉ።

ከዚህ ቀደም ተማሪዎች ምግብ ሳይበሉ ትምህርት ቤት ሲገቡ የማንቀላፋት፣ የመውደቅና መሰል ችግሮች ያጋጥሙ እንደነበር የሚገልጹት ወይዘሮ የምስራች፤ አሁን ላይ የምገባ መርሀ ግበሩ በመጀመሩ ተማሪዎች ጤናቸውን ጠብቀው ትምህርታቸውን በንቃት እየተከታተሉ እንዳሉ ተናግረዋል። በአሀገሪቷ ነባራዊ የኢኮኖሚ ሁኔታ ግን አቅርቦትና ክፍያው ተመጣጣኝ ባይሆንም፤ እናቶች በተባሉት ልክ ተማሪዎችን እየመገቡ እንዳለ ጠቅሰዋል።

ያለ ሥራ ቤት ውስጥ ይቀመጡ የነበሩና የሌላን ሰው እጅ ጠብቀው ይተዳደሩ የነበሩ በርካታ እናቶች በዚህ መርሀ ግብር የሥራ እድል ማግኘታቸውም ምገባው ከተማሪዎች አልፎ ለሌላውም ህብረተሰብ ጠቀሜታን የሰጠ መሆኑን ይገልጻሉ።

“ከእስከዳር፣ ቦሰናና ጓደኞቻቸው ማህበር” የተማሪዎች ምግብ አቅራቢ የሆኑት ወይዘሮ እስከዳር አበባው የምገባ መርሀ ግብሩ ከተማሪዎች አልፎ አቅራቢ እናቶችንም በስፋት የጠቀመ ነው ይላሉ። ሆኖም ግን ገበያውና የተመደበው በጀት ተመጣጣኝ እንዳልሆነ ይገልጻሉ። ምንም እንኳን የምግብ ዝርዝሩ ላይ የተቀመጡት ባይጓደሉም አቅርቦትና ፍላጎቱ ግን የሚመጣጠን ባለመሆኑ ፈታኝ መሆኑን ይናገራሉ።

ሥራው በሀገሪቱም ሆነ በከተማዋ አዲስ ነው የሚሉት አቶ ምነወር በበኩላቸው፤ በሌሎች ሀገራት የቆየና ብዙ ልምድ የተገኘበት እንደሆነ ያመላክታሉ። ቆየት ብለው በጀመሩ ሌሎች ሀገራት የአመራር ሥርዓቱም ሆነ የአደረጃጀት ሁኔታው የተሻለ መሆኑንና ኢትዮጵያ በልምምድ ውስጥ መሆኗን፤ እንዲሁም በሀገሪቱ በተቋማት ደረጃ ክፍተቶች መኖራቸውን ጠቅሰው፤ ነገር ግን ባለፉት ዓመታት የተሠሩ ሥራዎች የሚያሳዩት “ልምድ እንደሌለን አይደለም” ብለዋል።

በየጊዜው የሚታዩና በክትትልና በጥቆማ የሚገኙ ችግሮችን መረጃ በመውሰድ የአደረጃጀት፣ የአሠራር ማሻሻያዎች እየተደረጉ እንዳለ ገልጸዋል። በተመሳሳይ ደግሞ በዚህ ዘርፍ ተገቢ ያልሆነ ሥራ ውስጥ ተሳትፎ ያደረጉና ሥራውን ያጓደሉ እንዲሁም ሌሎች አሉታዊ ተግባራትን የፈጸሙ የትምህርት ቤት አመራሮችና አቅራቢ ማህበራት ላይ ርምጃ እየተወሰደ እንዲስተካከል መደረጉን አስታውቀዋል። ችግሮችን ለመቅርፍ በእያንዳንዱ ትምህርት ቤቶች የምግብ ሥርዓት ተቆጣጣሪዎች መቀጠራቸውንም ነው የጠቀሱት።

በየጊዜው የሚደረግ የምግብ ዝርዝር ማሻሻያዎች እንዳሉ የጠቆሙት አቶ ምነወር፤ የምግብ ይዘት ለተማሪዎቹ የተመጣጠነ ምግብ እንዲሰጥ ተደርጎ በጤና በለሙያዎች አማካኝነት መዘጋጀቱን ይናገራሉ። ከዚህ ጋር ተያይዞ ፈታኝ የሆነውና የምግብ ዝርዝርን ባለመከተል ጥራት የማጓደል ሁኔታዎች የሚያጋጥሙት ከቻልተኝነትና አጉል ጥቅም ፈላጊነት እንዲሁም አሁን ካለው የኢኮኖሚ ሁኔታ ጋር ተያይዞ የሚነሱ ጉዳዮች መኖራቸውን አብራርተዋል። ይሁን እንጂ ከተማ አስተዳደሩ ለአቅራቢ ማህበራቱ የሚያቀርበው ዋጋ ጥናትን መሠረት ያደረገ መሆኑንም ገልጸዋል።

በአንዳንድ ቦታዎች በምገባው ሂደት ላይ ከምግብ ዝርዝሩ መጓደልና የዋጋ ተመን ተመጣጣኝነት አኳያ የሚነሱ ቅሬታዎችን በተመለከተ፤ ችግሮቹ በማንኛውም መደበኛ ሥራ ላይ እንደሚያጋጥሙት አይነት እንጂ የተጋነኑ እንዳልሆኑ ጠቅሰው፤ ችግሮች ሲፈጠሩ በየጊዜው ድጋፍና ክትትል እየተደረገ እንዳለም አመላክተዋል።

“ከ447 ትምህርት ቤቶች በላይ ነው ይህ ሥርዓት ተፈጻሚ የሆነው። ከስፋቱ አንጻር የምግብ ዝርዝሩ በተወሰነ መልኩ በተቀመጠው ልክ ተፈጻሚ ላይሆን ይችላል። ከዚህ ውጭ በተጨባጭ በሚታይና በቁጥር ሊረጋገጥ በሚችል መልኩ እየተከናወነ ያለ ነው” ብለዋል።

በሥራው ላይ እየተሳፉ ያሉ ከ16 ሺህ ባላይ መጋቢ እናቶች፤ ከ690 በላይ ማህበራት ተጠቃሚ መሆናቸውንም ገልጸዋል። አልፎ አልፎ ከግለሰብ የሥነ ምግባር ጉደለትና ከመጋቢ እናቶች ችግር ምክንያት አለግባብ ሜኑ የማጓደል ውስን ጥፋቶች ሊያጋጥሙ እንደሚችሉ፤ አቅም እየዳበረ እንዲሁም የማህበረሰቡ ግንዛቤ እየሰፋ ሲመጣና ብዙኃኑ እየተሳተፉና አስተዋጽኦ እየበረከቱ ሲመጡ ችግሮቹ ተቀርፈው ጥራቱም አገልግሎቱም ቀልጣፋና የበለጠ ውጤታማ ይሆናል ነው ያሉት።

ኃላፊው እንደገለጹት፤ ከአቅራቢዎች በኩል የሚነሱ የዋጋ ተመን ያንሰናል ጥያቄዎች አሁን ላይ እየታዩ ባሉ የግብዓት ዋጋ ተለዋዋጭነት ምክንያት ሊሆን ይችላል። ከዚህ ውጭ ግን የዋጋ ተመኑ የተሠራው ጥናት ላይ ተመስርቶ ነው። የሚቀርበው እያንዳንዱ የምግብ አይነት ላይ የሚቀርበው የግራም መጠን ታውቆ የተሠራ ነው። መጋቢ እናቶችም ትርፍ የሚያገኙት ከብዛት ነው። የማህበራቱ የግዥ ሥርዓትና የማስተዳደር አቅም ውስንነት የሚፈጠረው ነገር ካልሆነ ከመንግሥት ከሚደረጉ ድጋፎች አንጻር ማለትም የግብር ተመን ዝቅተኛነት፤ ከዚህ ጎን ለጎን የተለያዩ ማህበራትን ግብዓት በቅናሽ እንዲያገኙ፣ ከአርሶአደሮች ጋር ትስስር እንዲፈጥሩ እየተደረገ ይገኛል።

ይህ ጅምር በኢትዮጵያ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ከተዘረዘሩት ሀገራዊ የልማት ስትራቴጂዎች ጋር የተጣጣመ ሲሆን፤ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የዘላቂ ልማት ግቦችን ለማሳካት ከሚደረገው ሰፊ ጥረት አንዱ አካል ነው። እ.ኤ.አ. በ 2022 የዓለም ባንክ ሪፖርት ፣ የትምህርት ቤት የምግብ ፕሮግራሞች ጤናማ እና የተሻለ የተማረ ሕዝብ በማፍራት ከድህነት አዙሪት የመውጣት አቅም አላቸው፣ ይህ ደግሞ የሀገሪቱን ኢኮኖሚያዊ ተስፋ ያጠናክራል።

# ከአፍሪካ ቀንድ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ለቀባሪ ማርዳት አይነት መሆኑ ነው።

የራሷ አሮባት የሌላውን ታማስላለች ነውና ነገሩ ሶማሊያም ብትሆን ያለባትን የውስጥ ችግር ከመፍታት ይልቅ ዳር ቆመው እሰይ አበጀሽ በሚሏት ድምጾች ተሸብባ ካፈርኩ አይመልሰኝ ብላለች። ምን ይሄ ብቻ «ሸሽታቹ በክረምትና በጭቃ አይሁን» የሚለውን የፈጣሪ ቃል የዘነጋችም ትመስላለች። በዚህም ታዲያ የግብፅን የእውር ድንብር ጉዞ ደግፋ ሀገሯን ይበልጥ ወደ ለየለት ቀውስ ውስጥ እያስገባች ትገኛለች።

ይህ አካሄድም ታዲያ ለአፍሪካ ቀንድ ስጋት መሆኑን የዘርፉ ሙሁራን ያብራራሉ። ከሁሉ የሚገርመው ይላሉ ሙሁራኑ የአፍሪካ ህብረትም ሆነ ኢጋድ በጉዳዩ ዙሪያ ዝምታን መምረጣቸው ጉዳዩን አሳሳቢ ያደርዋል።

በዲላ ዩኒቨርሲቲ የማህበራዊ ሳይንስና የሥነ-ሠብ ኮሌጅ መምህርና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአፍሪካና የኤሲያ ጥናት ሶስተኛ ዲግሪ ተማሪ ዳዊት መዝገበ ጸጋዬ ለኢፕድ በሰጡት ቃል፤ የጠላቴ ጠላት በሚል ግብፅ ከሶማሊያ ጋር እያደረገችው ያለው ስምምነት የሶማሊያን መንግሥት ፍላጎት የሚያሟላ ሳይሆን የግብጽን ቀጣናዊ የማተራመስ ፍላጎት ለማሳካት ያለመ ነው ይላሉ።

ግብፅ ለሶማሊያ የምታደርገው ድጋፍ አልሸባብን ከማስታጠቅም በላይ ሕገ-ወጥ የጦር መሣሪያ ዝውውር ነው የሚሉት መምህር ዳዊት፤ በዓለም ላይ የሚገኙ አሸባሪዎች ካላቸው ትስስር አንጻር ጦሱ ለአፍሪካ ቀንድ ብቻ ሳይሆን ለመላው ዓለም የሚተርፍ መሆኑን ይናገራሉ።

የግብፅ ዓላማ በዲፕሎማሲ ከሚያምንና የመንግሥት ቅርፅ ካለው አካል ይልቅ አልሸባብን እንዲሁም መሰል አሸባሪዎችን አስታጥቃ ለራሷ ጥቅም ለማዋል መሆኑን ያክላሉ።

ግብጽ ለሶማሊያ እያስታጠቀችው ያለው መሣሪያ ለአልሸባብ ተጨማሪ አቅም መፍጠር የሚችል ስለመሆኑም ያስረዳሉ። በዓለም ላይ እየተካሄዱ ባሉ ጦርነቶች ኃያላን ሀገራት ድጋፍ የሚያደርጓቸው መሣሪያዎች የት እንደሚገቡ ኦዲት ባለመደረጉ የአሸባሪዎች መበራከት ለዚህ ማሳያ ነው።

እንደ መምህር ዳዊት ገለጻ፤ በ1990ዎቹ ከሲያድባሬ ውድቀት ጀምሮ የሶማሊያ የሽግግር መንግሥት እንዲቋቋም ኢትዮጵያ ትልቁን ሚና ተጫውታለች። የአፍሪካ ቀንድ የጦር መሣሪያ እጥረት የለበትም፤ ለቀጣናው የሚቆረቆር አካል መሠረተ ልማት እንጂ መሣሪያ መስጠት ትክክል እንዳልሆነ ይታወቃል።

ግብጽ ከአረብ ሀገራት የበለጠ ለአፍሪካ ትኩረት ሰጥታ አታውቅም የሚሉት መምህር ዳዊት፤ በአፍሪካም ሆነ በአፍሪካ ቀንድ ሰላም ማስከበር አለመቻሏ ብቻ ሳይሆን ሌሎች በየጊዜው መስዋዕትነት ሲከፍሉ የነበሩ ጎረቤት ሀገራት የት ሄደው ነው ሲሉም ይጠይቃሉ።

መምህር ዳዊት፤ በተለይ አፍሪካ የጸጥታው ምክርት ቤት አባል አለመሆኗ በአህጉሪቱ ባላንጣነት እየተስፋፋ መሆኑን ጠቅሰው፤ቀጣናው በባህል፣ በቋንቋ እንዲሁም በሃይማኖት የሚያገናኛቸው በርካታ ጉዳይ በመኖሩ ከጦርነት ይልቅ ዲፕሎማሲው የበለጠ ዘላቂ ውጤት የሚያመጣ መሆኑን ያብራራሉ።

በግብፅ እንቅስቃሴ ዙሪያ የአፍሪካ ህብረት ድክመት አለ ያሉ ሲሆን ግብጽ አፍንጫዋ ስር ያለውን ሰላም ማስከበር ሳትችል ወደ አፍሪካ ቀንድ መጥታ ሰላም ላስከብር ስትል በዝምታ ሊታለፍ አይገባም ባይ ናቸው።

በተጨማሪም ለአፍሪካ ችግር አፍሪካዊ መፍትሔ በሚለው መርህ ዲፕሎማሲ ፈጥሮ መፍትሔ መስጠትና ሕጋዊ ርምጃ መውሰድ የሚያስፈልገውን ደግሞ ሕጋዊ ርምጃ መውሰድ እንዳለበት ይናገራሉ።

የግብፅ እንቅስቃሴ ለአየር መንገዶችና የባህር ላይ ንግዶች ላይ ከፍተኛ ሳንካ የሚፈጥር ከመሆኑም በላይ ለሕገ-ወጥ የሰዎች፣ ንግድ፣ ገንዘብና የመሣሪያ ዝውውር መናኸሪያ ለሆነችው ሶማሊያ ተጨማሪ ስጋት የሚጭር ነው።

የኢንቴራክሽን ፎር ቼንጅ ኢን አፍሪካ ዳይሬክተር ወርቁ ያዕቆብ (ዶ/ር) በበኩላቸው ግብፅ ለሶማሊያ መንግሥት የምታደርገውን የጦር መሣሪያ ድጋፍ ለአልሸባብ ተጨማሪ ጉልበት ይሆናል የሚል ግምት ባይኖራቸውም በሶማሊያና ኢትዮጵያ መካከል ያለው ውጥረት የበለጠ የሚያባብሰው እንደሆነ ይጠቁማሉ።

ግብፅ፣ ሶማሊያና ኤርትሪያ በጋራ ጉዳዮቻቸው ላይ አብረው መሥራታቸው በራሱ ምንም ዓይነት አንደምታ ባይኖረውም በተለይ ከዚህ በፊት ያልተለመዱ የጦር መሣሪያ ስምምነቶችና ኢትዮጵያና ሶማሊያ ውዝግብ ውስጥ በገቡበት ወቅት መሆኑ የፖለቲካ ቁማር እንዳለ እንደሚጠቁም ያብራራሉ።

እንደ ዶክተር ወርቁ ገለጻ፤ ጠብታ የዓባይን ውሃ በብቸኝነት የመቆጣጠር ፍላጎት ያላት ግብፅ ፍላጎቷ ከዚህ ቀደም በነበረው ዲፕሎማሲ መንገድ ማሳካት ሲሳናት ቀጣናውን በማተራመስ የጀመረችው የፖለቲካ ቁማር ነው። የግብፅ ሌላኛው ዓላማ በውክልና ጦርነት የኢትዮጵያ መንግሥት ኃይል ተዳክሞ ህዳሴ ግድብ ላይ ያለውን ትኩረት እንዲቀንስ ለማድረግ ነው።

የኢትዮጵያ መንግሥት ቆም ብሎ ውሳኔዎችን በጥንቃቄ ከወሰደ እንዲሁም ስለጉዳዩ በቂ ግንዛቤ መፍጠር ከቻለ የሦስቱ ሀገራት ስምምነት የሚያሳድረው ጫና የለም።

የግብፅ አጀንዳ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለመዝጋት የህዳሴ ግድብ በሁሉም ዘርፎች በሙሉ አቅሙ ወደ ምርት እንዲገባና ኤሌክትሪክ የሚወስዱ ሀገራት በሙሉ አቅም እንዲሰጥ ማድረግ ተገቢ ነው የሚሉት ዶክተር ወርቁ፤ የህዳሴው ግድብ ይጠናቀቃል በተባለው ጊዜ ባለመጠናቀቁ ለግብፅ የፖለቲካ ቁማር በር ከፍቶ መቆየቱን ተናግረዋል።

# ኢትዮጵያ የምታካሂዳቸው...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ማካሄድ ተችሏል።

እንደ ዘለቀ (ዶ/ር) ገለጻ፤ የቢዝነስና የኢንቨስትመንት ጉባዔዎች የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰቱን የመጨመር ዕድል አላቸው። ያለፈው የ2017 ሩብ ዓመት ከ2016 ተመሳሳይ ዓመት ጋር ሲነጻጸር የ12 በመቶ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ጭማሪ አለው።

የኢትዮ- አስትሪያ የቢዝነስ ጉባዔ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ለማሳደግ ታስቦ የተዘጋጀ መሆኑን ጠቁመው፤ በጉባዔው ለመሳተፍ ከኦስትሪያ የሚመጡ ባለሀብቶች በኢትዮጵያ እንዲያለሙ በማድረግ ፍሰቱን ለመጨመር ታሳቢ ተደርጎ እየተሠራ ነው ብለዋል።

በአይነቱ ለየት ያለ የቢዝነስ ጉባዔ ከኦስትሪያ ጋር ይካሄዳል ያሉት ምክትል ኮሚሽነሩ፤ ትላልቅና ረጅም ዓመት ልምድ ያላቸው ድርጅቶች ወደ ኢትዮጵያ እየገቡ ነው። ይህም ኢትዮጵያ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ፍሰትን እንዲሰፋ እያስቻለ ነው። ኮሚሽኑ በውጭ ሀገር በተዘጋጁ ጉባዔዎች ላይ በንቃት በመሳተፍ የተወሰኑ አልሚዎችን መሳብ ችሏል። በ2017 በእቅድ ደረጃ የተያዙ በርካታ የንግድና የቢዝነስ ጉባዔዎች መኖራቸውን ጠቅሰዋል።

በኢትጵያና በኦስትሪያ መካከል ጠንካራ ዲፕሎማሲዊ ግንኙነት አለ ያሉት ምክትል ኮሚሽነሩ፤ አንድ መቶ ዓመት ያስቆጠረ ጠንካራ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ነው። በዲፕሎማሲው ረገድ ያለውን ጠንካራ ግንኙነት በኢኮኖሚ ረገድ መድገም ተገቢ በመሆኑ የቢዝነስና የኢንቨስትመንት ጉባዔው መዘጋጀቱ አስፈላጊ ነው። በጉባዔው የሚሳተፉ ድርጅቶች በተለያዩ ዓለም አቀፍ ሀገሮች ልምድ ያላቸው መሆናቸውንም ጠቅሰዋል።

ለውጭ ቀጥታ ኢንቨስትምንት መጨመር ብዙ ምክንያቶች አሉ ያሉት ምክትል ኮሚሽነሩ፤ በቅርቡ የወጣው



የልዩ ኢኮኖሚ አዋጅ ወደ ሥራ ገብቷል። አዲሱ አዋጁ በሀገር ያሉ ኢንዱስትሪያል ፓርኮችን ወደ ልዩ የኢኮኖሚ ዞን የሚያሸጋግር ሲሆን የማዘዋወር ሥራው ተጀምሯል። ይህ ደግሞ ለሀገርና ለውጭ አልሚዎችምች ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር መሆኑን አብራርተዋል።

ባለፈው ሳምንት አራት ድርጅቶችን ከኢንዱስትሪ ፓርክ ወደ ልዩ የኢኮኖሚ ዞን እንዲሸጋገሩ ማድረግ መቻሉን በመጥቀስ የተደረገው የኢንቨስትመንት ፖሊሲ ማሻሻያ ለውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት መጨመር ሌላው ምክንያት ነው ብለዋል።

ኢትዮጵያ የኦስትሪያ አምባሳደር ሲሞን ኬናፕ (ዶ/ር) በበኩላቸው፣ የቢዝነስ ጉባዔው ለሁለቱም ሀገራት ትልቅ ጠቀሜታ አለው። ኢትዮጵያና ኦስትሪያ ረጅም ጊዜን ያስቀጠረ የዲፕሎማሲ ግንኙነት አላቸው። በቅርብ ጊዜ ደግሞ በንግድ ዘርፍ ያላቸው ግንኙት መጠናከሩን ጠቅሰዋል።

ግንኙነቱ አንድ መቶ ዓመትን የተሻገረ ሲሆን፤ በአዲስ አበባ የኦስትሪያ ኤምባሲ የተከፈተበትን 60ኛ ዓመት እንደሚከበርም ጠቅሰዋል።

የኦስትሪያ ኩባንያዎች በኢትዮጵያ በተለያዩ ዘርፎች መሰማራት ይፈልጋሉ ያሉት አምባሳደሯ፣ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቱን አስመልክቶ የኦስትሪያ አልሚዎች በኢትዮጵያ እንዲያለሙ ለማድረግ የቢዝነስ ጉባዔ ተዘጋጅቷል። የኦስትሪያ ባለሀብቶች ኩባንያዎቻቸውን በኢትዮጵያ የማስፋት እቅድ አላቸው፤ ቢዝነስና የንግድ ጉባዔ ለአልሚዎች ትልቅ እድል ይፈጥራሉ። የኢንቨስትመንት ማሻሻያዎችና መንግሥት እየተገበረ ያለው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ለአልሚዎች ትልቅ እድል እንደሚፈጥር ገልጸዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ለሰላም ጊዜው አልረፈደም

የሰላምን ዋጋ በተጨባጭ የሚያውቅ ግለሰብ ሆነ ማህበረሰብ በሰላም እጦት ውስጥ ያለ ወይም በታሪክ አጋጣሚ ስለ ሰላም ብዙ ዋጋ ለመክፈል የተገደደ ነው ። ከዚህ ውጪ ስለ ሰላም በመዘመር ሆነ ብዙ በማውራት ዋጋውን ማወቅ አይቻልም ። በዚህ መልኩ የሰላምን ዋጋ ለመገመት የሚደረግ የትኛውም አይነት ጥረት የተሟላ ሊሆን አይችልም ።

እኛ ኢትዮጵያውያን ካሳለፍናቸው የሰላም እጦት ዘመናት እና ከሰላም እጦት ጋር በተያያዘ በየዘመኑ ለመክፈል ከተገደድነው ያልተገባ ዋጋ አንጻር ፤ የሰላም ዋጋ ምን ያህል እንደሆነ አውቆ እና ተረድቶ ለመገመት ሆነ በተጨባጭ ለመናገር የሚከብደን አይደለም ። የሄደውም ፣ ያለው ሆነ የሚመጣውም ትውልድ ስለሰላም ዋጋ ከማንም በላይ መናገር ይችላል።

በአንድ በኩል የሰላምን ሁለንተናዊ ዋጋ ከፍ አድርገው በሚያስተምሩ መንፈሳዊ ፣ ማህበራዊ እና ባህላዊ እሴቶች ውስጥ ማለፋችን ፤ ከዛም ባለፈ በየዘመኑ የነበሩ ትውልዶች ከሰላም እጦት ጋር በተያያዘ ሕልሞቻቸውን ኖረው ማለፍ አቅቷቸው ፤ ህልሞቻቸውን ከሩቅ ተሳልመው የማለፋቸው እውነታ የሰላም ዋጋ የቱን ያህል እንደሆነ ለመገመት ፈተና አይሆንብንም ።

በርግጥ እያንዳንዱ ትውልድ ዘመኑን የሚመጥን የመለወጥ /የለውጥ አስተሳሰብ ባለቤት ነው። ይህን የለውጥ አስተሳሰብ ስጋና ደም አላብሶ ሕይወት እንዲዘራ ለማድረግ ከሁሉም በላይ ሰላም ያስፈልጋል። ያለ ሰላም እንኳን ነገን ፣ ዛሬን ፤ የሚቀጥሉትን ደቂቃዎች በእርግጠኝነት ማሰብ አይቻልም።

ስለሚቀጥሉት ደቂቃዎች በእርግጠኝነት ማሰብ የማይችል ትውልድ ደግሞ በየትኛውም መንገድ ስለ ሀገሩ /ማህበረሰቡ ማሰብ የሚያስችለውን አቅም ሊፈጥር አይችልም ፤ ይህ ደግሞ የትውልዶችን ወጥቶ መሄድ ትርጉም አልባ ከማድረግ ባለፈ፤ በትውልዶች መተካካት ውስጥ ሊኖር የሚገባውን የመለወጥ መነቃቃት ይገድለዋል ።

የለውጥ መነቃቃት የሌለው ትውልድ ትናንት ውስጥ እንዲኖር የሚገደድ ነው ፤ የትናንቶች አድናቂ እና አፍቃሪ በመሆን የራሱን ዛሬዎች የሚያባክን ነው ፤ የትናንት ታሪክ ተራኪ እንጂ የራሱን ታሪክ የማይሠራ ፤ ራስ ወዳድ እና ጠባቂ ትውልድ መሆኑ የማይቀር ነው ።

በትውልዶች መካከል የሚኖር የሰላም እጦት በቀጥታ ሀገር እና ሕዝብን ከሚያስከፍለው ሞት ፣ ስደት ፣ መፈናቀል እና የንብረት ውድመት በተጨማሪ በትውልዶች መካከል ሊኖር የሚገባውን ቅብብሎሽ በመፈታተን ፤ ማህበረሰባዊ የአስተሳሰብ ልቀትን ፤ ከዚህ የሚመነጭ የለውጥ መሻትን ያደበዝዛል ።

ከዚህም ባለፈ ፤ ለድህነት እና ኋላቀርነት የሚዳርግ ፤ ሀገር እንደሀገር በዘመናት ያካበተችውን ሞገስ በማደብዘዝ ፤ ብሄራዊ ክብርን በማጉደፍ አንገት የሚያስደፋ ነው። በዚህም ማንነትን እስከመጥላት ለሚያደርስ የሥነልቦና ቀውስ የሚዳርግ ጭምር ነው።

ይህ እውነታ በየዘመኑ እንደሀገር አደባባዮቻችንን የሞሉ የለውጥ ፍላጎቶች ፤ በፍላጎቶቹ ውስጥ ዘር የነበሩ የነገ ብሩህ ተስፋዎች እንዲመክኑ አድርጓል ። ከእያንዳንዱ የታሪክ ምእራፍ ትውልዶች ተገቢውን ትምህርት መውሰድ አቅቷቸው በተመሳሳይ የታሪክ ጉዞ ውስጥ ዋጋ ለመክፈል ተገድደዋል።

እንደ ሀገር ስለሰላም በየዘመኑ ብዙ ያልተገባ ዋጋ እየከፈልን ፤ ከምንከፍለው ዋጋ መማር አለመቻላችን የታሪካችን ሆነ የማህበረሳባዊ ማንነታችን ተጠየቅ ሆኗል ። ስለ ሰላም አብዝተን እየዘመርን ፤ ስለሰላም በብዙ አስተምሮ ውስጥ እያለፍን የሰላም ዋጋ ተረድተን በተጨባጭ ለሰላማችን ዘብ መቆም አለመቻላችን የዘመናት እንቆቅልሻችን አካል ነው ።

ዛሬም ላይም ቢሆን እየሆነ ያለው ከትናንቶች የተለየ አይደለም ። እንደ ማህበረሰብ በትልቅ የለውጥ መነቃቃት ውስጥ ነበርን ፤ መነቃቃታችን እንደቀደሙት የለውጥ ዘመናት በሰላም እጦት ምክንያት እለት እለት እየተፈተነ እንደ ትውልድ ተስፋ ያደረግናቸውን ብሩህ ነገዎች እያደበዘዘ ነው።

በብዙ ሀገራዊ መነቃቃት አደባባይ ሞልቶ የነበረው የትውልዱ የለውጥ መሻት፤ ትውልዱ ሰላሙን አስጠብቆ ማስቀጠል ባለመቻሉ እንደቀደሙት ትውልዶች የለውጥ መሻቱ በብዙ ፈተናዎች ውስጥ እየተንገጫገጨ ነው ። ያልተገባ ዋጋ እንዲከፍልም እያስገደደው ነው ።

በተለይም ተፈጥሯዊ የለውጥ መነቃቃቱን ጠልፈው ለግል እና ለቡድን የፖለቲካ ህልማቸው ግብአት ለማድረግ ያደቡ ሃይሎች ፤ ቋንቋውን እየተናገሩ ፤በስሙ እየማሉ እየተገዘቱ ፤ በማንነቱ እየፎከሩ ፤ ከማህበረሰባዊ ማንነቱ አጣልተው ለገዛ ሰላሙ ጠላት ሆኖ ዋጋ እንዲከፍል እያደረጉት ነው።

በየለውጥ የታሪክ ምእራፋችን የሚያጋጥመንን ይህንን ሀገራዊ ፈተና ለመሻገር ፤ ሰለማችንን ጠብቀን ለማስቀጠል ፤ በመዘናጋታችን ከከፈልነው ያልተገባ ዋጋ ብዙ ተምረን ፤ በሰላማችን ላይ ያነሳነውን ጠበንጃ አውርደን ተስፋችንን ተጨባጭ ለማድረግ ከቀደመው ትውልድ ብቻ ሳይሆን ከራሳችን የትናንት ታሪክ ተምረን ልንመለስ ይገባል ። ለዚህ ደግሞ ጊዜው አልረፈደም !


## አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፦ 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

## የቅኝ ግዛት ውሎችን ወደ መቃብር የሸኘ ታሪካዊ ስምምነት !

አዶኒስ (ከሲኤምሲ)

"ዓባይ ማደሪያ የለው ግንድ ይዞ ይዞራል፤ ዓባይ ግብጽን እንጂ ምን ጠቀመ ለሀገሩ ፤ ዓባይ ዘፈን እንጂ አልሆነም እንጀራ፣ ዓባይ ለም አፈሩን ጠርጎ ሲና በረሃን ያበለጽጋል..." እየተባለ በዘፈንም በግጥም በየዘመናቱ ሲተችና ሲወቀስ ኖሯል። ዛሬም ቢሆን ከዓባይ እየተገኘ ያለው ጥቅም ዓባይን በጭልፋ እንደሚባለው ነው።

ሀገራችን ለረጅም ዓመታት የወንዙን ውሃ ለማልማት የተለያዩ ጥረቶች አድርጋለች ፤ ጥረቶቿ ቅኝ ገዥዎች ለራሳቸው ጥቅም ባስቀመጧቸው ኢትዮጵያን ያላካተቱ የክልከላ ውሎች ምክንያት ተግባራዊ መሆን ሳይችል ቀርቷል።

እነዚህ ለወንዙ ከፍተኛውን ውሃ የምታበረክተውን ሀገራችንን ያላካተቱ የቅኝ ግዛት ውሎች ፤በዓባይ ወንዝ ላይ ለኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ የሚውል ግድብ ለመገንባት የመሠረት ድንጋይ ካስቀመጠችበት ጊዜ ጀምሮ ትልቅ ፈተና ሆነው ቆይተዋል።

በነዚህ ውሎች ምክንያት ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት ለሥራው የሚሆን ብድር ከመከልከል ባለፈ፤ ግንባታውን ለማስተጓጎል ባፉት አስር ዓመታት ከፍተኛ የሆነ የዲፕሎማሲ ጫናዎች ሲደረጉ ቆይተዋል ። ከጫና ያለፉ ሴራዎች ሲደረጉ ቆይተዋል።

በተለይም በወንዙ ውሃ ፍትሃዊ ተጠቃሚነት እንዳይሰፍን ፤ ዘመን ያለፈባቸውን የቅኝ ግዛት ውሎች የሙጥኝ ያለችው ግብጽ ፤ ኢፍትሃዊነትን በዓለም አቀፍ አደባባዮች ድምጿን ከፍ አድርጋ ስታሰማ ፤ ለያዥ ለገላጋይ በማይመች መንገድ ያዙኝ ልቀቁኝ ስትል ተስተውላለች።

የኢትዮጵያ መንግሥትና ኢትዮጵያውያን የወንዙን ፍትሃዊ ተጠቃሚነታቸውን ታሳቢ ባደረገ መንገድ በዲፕሎማሲም ከፍ ያሉ ሥራዎችን በመሥራት ፤ አንድም የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ውሎች ዘመናቸው እንዲያበቃ ፤ በሌላ በኩል የግድቡን ሥራ ከፍ ባለ ቁርጠኝነት ሲያከናውኑ ቆይተዋል።

የግድቡን ሥራ በራሳቸው ገንዘብ፣ ጉልበትና እውቀት ተጨባጭ በማድረግ ፤ በወንዙ ውሃ ፍትሃዊ ተጠቃሚ የሚያደርጋቸውን አዲስ የታሪክ ምእራፍ በብዙ ፈተና ውስጥ ሆነው መጻፍ ችለዋል ። ሥራው አሁን ያለው ትውልድ እንደ ትውልድ በአንድ ድምጽ ሆ! ብሎ የሠራው፤ የሀገራዊ የጋራ ትርክቱ አካል ነው።

የአፍሪካ ሀገሮች በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ በተለያየ የቅኝ ግዛት ውሎች የታሰሩ ፣ በዓለም አቀፍ ሕግ ሳይቀር ተጠቃሚ የሚያደርጓቸውን መብቶቻችውን መጠቀም እንዳይችሉ በብዙ ክልከላ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ናቸው ። በተፈጥሮ ሀብቶቻቸው እንደልባቸው እንዳያዙና እንዳይጠቀሙ በኢ-ፍትሃዊነት የታሰሩ ናቸው። ከእነዚህ ሀገራት መካከል አንዷ ኢትዮጵያ ናት።

ኢትዮጵያ ከአፍሪካ ሀገራት በቅኝ ግዛት ካልተያዙ ሀገሮች ብቸኛዋ ትሁን እንጂ የተለያዩ ሕጎች በቀጥታም ባይሆን በተዘዋዋሪ መልኩ የቅኝ ግዛት ተጽእኖ አርፎባታል። በዚህም በዓባይ ወንዝ ላይ ያላትን የባለቤትነት መብት ፍትሃዊ በሆነ መንገድ መጠቀም እንዳትችል ተደርጋ ቆይታለች።

ሀገሪቱ ለናይል ወንዝ ከፍተኛውን የውሃ መጠን ብታበረክትም ፤ ከውሃ ሀብቱ ተጠቃሚ ሳትሆን የበይ ተመልካች ሆና ለዘመናት ቆይታለች። በውሃ ሀብቱ ላይ ምንም አይነት መብት እንዳይኖራትም ባልተስማማችባቸው የቅኝ ግዛት ውሎች ታሥራ ቆይታለች ።

ይህም ሆኖ ኢትዮጵያ በዓባይ ወንዝ ላይ የፍትሃዊ ተጠቃሚነትና በውሃ ሀብቱ እኩል ባለመብትነት እንዲኖራት ከፍተኛ የዲፕሎማሲ ሥራዎችን ስትሠራ ቆይታለች። በዚህም አሁን ላይ ውጤታማ መሆን ችላለች።

ሀገሪቱ ከጎረቤት ሀገሮች ጋር በሰላም በጋራ ተጠቃሚነት ላይ የተመሰረተ የውጪ ፖሊሲን የምትከተል ከመሆኗም አኳያ ፤ የናይል ውሃን በፍትሀዊነት ለመጠቀም በተፋሰሱ ሀገራት በሚደረገው ጥረት ውስጥ የጎላ አስተዋጽኦ ስታበረክት ቆይታለች ።

**የኢትዮጵያ መንግሥትና ኢትዮጵያውያን የወንዙን ፍትሃዊ ተጠቃሚነታቸውን ታሳቢ ባደረገ መንገድ በዲፕሎማሲም ከፍ ያሉ ሥራዎችን በመሥራት ፤ አንድም የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ውሎች ዘመናቸው እንዲያበቃ፤ በሌላ በኩል የግድቡን ሥራ ከፍ ባለ ቁርጠኝነት ሲያከናውኑ ቆይተዋል**

በርግጥ ሀገሪቱ የዓባይ ግድብን ለመገንባት የተነሳችው የታችኛው ተፋሰስ ሀገራትን ውሃ ለማሳጣት አስባ ሳይሆን ከ60 በመቶ በላይ የኤሌክትሪክ ሃይል ተጠቃሚ ያልሆኑ ዜጎቿን የኤሌክትሪክ ሃይል ተጠቃሚ ለማድረግ ነው ፤ ይህ ደግሞ ከሞራልም ከዓለም አቀፍ ሕግም አንጻር ተቀባይነት ያለው ነው።

ይህንን የዓደባባይ እውነታ በማጣመም ጉዳዩን ዓለም አቀፍ አጀንዳ ለማድረግ የግብጽ መንግሥት ረጅም ርቀት ተጉዟል ፤ ጉዳዩን ለጸጥታው ምክር ቤት ከ15 ጊዜ በላነሰ አጀንዳ ለማድረግ ሞክሯል ። በጉዳዩ ዙሪያ በያዘችው የዲፕሎማሲው የበላይነት እነሆ ታላቁ ህዳሴ ግድብን ከመገንባት አልፎ በሁለተኛ ዙር ሃይል የማመንጨት ተግባር ላይ ተደርሷል።

አሁን ላይ ግብጽም ሆነች ሌሎች የተፋሰሱ ሀገራት ምንም አይነት የውሃ እጥረት ሳይገጥማቸው ውሃው ኤሌክትሪክ አመንጭቶ በበቂ ሁኔታ ለታችኞቹ የዓባይ ተፋሰስ ሀገራት መድረስ ችሏል። ዛሬም የውሃ መጠኑ ምንም ሳይቀንስ ማግኘትና መጠቀማቸውን ቀጥለዋል።

ከዚህም ጎን ለጎን የናይልን ውሃ በፍትሃዊነት ለመጠቀም ለረጅም ዓመት ሲደረግ የነበረው ትግል የናይል የትብብር ማዕቀፍ ስምምነት ተግባራዊ ወደሚሆንበት የታሪክ ምእራፍ ተሸጋግሯል። አዲሱ የትብብር ምዕራፍ የተፋሰሱ ሀገራት የወንዙን ውሃ በፍትሃዊነት ለመጠቀም ፣ የውሃውን ደህንነት በጋራ ለመጠበቅ፣ እንዲሁም ለሁሉም መብት እኩል እውቅና የሚሰጥ ነው ።

በቀጣይ ይሄንን የሚያስተዳድር ኮሚሽንና የጋራ የሕግ ማዕቀፍ ይዘጋጃል። በዚህ የሕግ ማዕቀፍም ሁሉም እኩል መብትና ጥቅም ኖሯቸው በጋራ ሀብቱ የሚለሙበት እድል ይፈጠራል ተብሎ ይጠበቃል። ኢትዮጵያም ይህንኑ ፍትሃዊና የጋራ ተጠቃሚነትን መርህ ወደፊት ባስቀደመ መልኩ የወንዙ ውሃ ተጠቃሚ ትሆናለች ።

በስድስት የተፋሰሱ ሀገራት የተፈረመው የትብብር ማዕቀፉ ከዚህ በፊት በናይል ወንዝ ውሃ አጠቃቀም ላይ የነበረውን በኢ- ፍትሃዊነትን የታሰሩ የቀኝ ግዛት ውሎችን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ማስወገድ የሚያስችል ነው ። በቀጣይም ለስምምነቱ ተግባራዊነት ፊርማቸውን ያላኖሩ ሀገራትም ፤ የቅኝ ግዛት ውሎች ዘመኑን የማይዋጁና የትም የማያደርሱ መሆናቸውን ተገተንዝበው ስምምነቱን በመፈረም ለፍትሃዊነት ያላቸውን ቁርጠኝነት በአደባባይ ያሳያሉ ተብሎ ይጠበቃል ።

# ነፃ ሃሳብ

# ለሀገር አቅኚ ምክረ ሀሳቦች እንገዛ

**ቴዎጌዎቴዎፌዎሶር (የኩሽ አሽከታብ)**

ሀገር አቅኚ መወከረ ሀሳቦች በዘመን ስለተደገፉ አእምሮና ልቦች ሳይሆን ስለሚበልጥ እውነት የሚያወጉ የቁም ነገር መድረኮች ናቸው። ለተሻለ የሀገረ መንግስት ግንባታ የተሻለ ሀሳብ የሚዋጣበት፣ ልዩነቶቻችንን ለጦርነት ሳይሆን ለአዋጭ ሃገራዊ ትርክት የምንጠቀምበት፣ በቆዩና በነበሩ እሴቶቻችን አብሮነትን አዳብረን ስለአንዳንድ አለመግባባቶች መላ የምንዘይድበት የኢትዮጵያውያን የማሰብና የማሰላሰል መድረክ ነው።

እየሆንን ያለነውና እየሆነብን ያለው ግን በተቃራኒው ነው። ሀሳቦቻችን ጥል አዝለው በቀልን ከወለዱ ሰነባብተዋል። ለሸንጎ ያልደረሱ ትንንሽ ጣጣዎች ለአፈሙዝ ሲያበቁን ማየት ምን ነካን? ምን እየሆንን ነው? ከሚሉ ጥያቄዎች በገዘፈ ነገን እንድንሰጋ የሚያደርጉን ናቸው። ከማንም ቀድሞ ባለሀገር የሆነ ሕዝብ፣ ከማንም ቀድሞ መተዳደሪያ ስርዐት የመሰረተ ማንነት፣ ነጻነትና ሰብዐዊነት፣ ሰላምና አስታራቂነት በስሙ የሚገነኑበት ሕዝብ ነበርን አሁን ግን .... ለምን ? ።

አሁን እንደሀገር እየሆነው ስላለው ነገር ለምን ብለን የምንጠይቅበት ወቅት ላይ ነን። መታወቂያችን የነበሩት ሰላምና ፍቅር፤ በእርስ በርስ ትስስር ያበለጸጉን የወንድማማችነት ካባዎቻችን የት ነው ያሉት ? በስመ ሀበሻ የሚጠራ ማንነታችን ጥላቻን በሚሰብኩ በማይረቡ ተራ ስሞች ተቀይሮ መነሻችንን ከልሎብናል። አንድ መልክን ሰጥተው በአንድ አምሳል ያበቀሉን እሴቶቻችን እንድንፈራራ እና እንድንሰጋጋ በሚያደርግ የፖለቲካ እድፍ ቆሽሸው ጥላቻ ነጋሪ ሆነዋል።

ሀገር በሰላም እና በጦርነት ስትታወቅ አንድ አይደለችም። የመጣንበትን ረጅም መንገድ ትላንትና ዛሬ ብለን በሁለት ብንከፍለው የሰላምና የጦርነት ዘመን ብለን እንመድበዋለን። እርግጥ ጦርነት ለረጅም ዘመን አብሮን የመጣ መጥፎ ታሪካችን ሆኖ የሚወሳ ቢሆንም ከአሁናዊ ጀብደኝነታችን ጋር ሲነጻጸር ምን እና ምን ነው የሚያስብል እየሆነ ነው።

ቀደም ሲል በክብራችንና በሉአላዊነታችን ከመጡት የውጪ ኃይላት ጋር ነበር፤ አሁን ግን ነጻ አውጪ በሌለው የእርስበርስ ጦርነት ላይ ነን። ድሮ ለነጻነትና ለመላው የጥቁር ሕዝብ ስንል አትንኩኝ ብለናል አሁናዊ ጀብደኝነታችን ግን ፖለቲካ ወለድ የሀሰት ትርክት ነው። እንዲህ አይነቱ የእርስ በርስ ፍትጊያ ሀገር አቅኚ ምክረ ሀሳብ ያስፈልገዋል።

በሀሳብ የዳበረ ፖለቲካ ሀገርን ያስቀድማል። ሀሳብ ሀገር ይፈጥራል፣ ትውልድ ይቀርጻል በስተመጨረሻም ለእርቅና ለምክክር ደጃፉን የከፈተ ማህበራዊ ልምምድን ይሰጠል። በእኛ አሁናዊና የከርሞ የፖለቲካ ማዕቀፍ ውስጥ ግን ይሄ አይነቱ ልምምድ የለም። ለምንም ነገር ኃይልን አስቀድመን ከተቻለ በውዴታ ካልተቻለ በግዴታ ነገሮችን በማስፈጸም ልምምድ የመጣን ነው። ይሄ ብልሹ ልማድ አድጎ ፖለቲካው ለሀገር እንዳይጠቅም፣ ፖለቲከኞቻችንም ለትውልድ እንዳይበጁ ከማድረጉ እኩል ደምን በደም አስተሳሰብን አስርጾብናል።

የሚበጀን ደምን በደም ሳይሆን ደምን በእርቅ ነው። እርቅ ደም ያድርቅ በሚል ማህበራዊ ስነቃል በሸንጎና በሽምግልና በዛፍ ጥላ ስር ተጠልለን፣ በነጭ ቡሉኮ ጭራችንን ግራና ቀኝ እያወናጨፍን፣ በዳበረ የአንተም ተው አንተም ተው ወግ ጥልና ጸቦችን አብርደን ብርቱ ማህበራዊ ስርዐትን አንጸናል።

በታላቁ አባት በፈጣሪ ስም፣ ይቅር ለእግዜር› በሚል አስታራቂ ምሬት ጥላቻዎቻችንን ወደፍቅር ቀይረን አብሮነታችንን አስምረናል። ዛሬ ላይ እነዛ የሀገር ጌጥ፣ የትውልድ መልኮች የት ጠፉ ብለን ስንጠይቅ አንድም ዘረኝነት ሸሽጓቸዋል አንድም ፖለቲካው አጥቁሯቸዋል። ሌላ ምክንያት ካስፈለገም ለጥላቻና ለእርስ በርስ ውንብድና የሚወግኑ ክፉ ትርክቶች አወይበዋቸዋል።

ወደነበርንበት የዛፍ ጥላ ስር መመለስ፣ ወደነበርንበት የእርቅ ማዕድ ማስተዋላችን፣ በይቅር ለግዜር ስም ጥላቻዎቻችንን የመሻራችን ማህበራዊ ልምምድ ሀገር የምትፈጠርበት፣ አንቂ ምክረ ሀሳቦቻችን የሚያቆጠቁጡበት እንዲሁም ከእርስ በርስ ፉክክር ወደእርስ በርስ ምክክር የምንመጣበት የአዲስ አስተሳሰብ መንገድ ጠራጊ እንደሚሆን በጽኑ አምናለው። አሁን ላሉብን ዘርፈ ብዙ የውስጥና የውጪ ችግሮች በሀሳብ የተሞላ ፖለቲካና ፖለቲከኛ ያስፈልገናል።

በሀሳብ ባልበረታ ማንነት መሀል ሆነን ትላልቅ ሀገራዊ ራዕዮችን ብናርይ ትርጉም የለውም። ሀገራት በኢኮኖሚና በስልጣኔ በርትተው የሚታዩት ሀገር ቀራጭ የሆነውን ፖለቲካ በሀሳብ መምራት ስለቻሉ ነው። ሀምሳ እና ስልሳ ዓመታትን ያለማቋረጥ ጦርነት ያካሄድን ሀገራት ነን። በነዚህ ዓመታት ውስጥ ምን እንዳጣን እንኳን ለማሰብ ጊዜ አጥተን በተመሳሳይ ጥፋት ውስጥ ነን። ማሰብ የሚለው ልዕለ ኃይል ዋጋ ያለው ሆኖ የሚገለጠው እንዲህ ባለው አጥፊ ታሪክ በኩል ነው።

እስኪ ለአፍታ ወደጦርነት የወሰዱንን የፖለቲካ ንትርክም ሆኑ የሀሰት ትርክቶች እንቃኛቸው። ችግሮቻችንን በውይይት ፈተናቸው ቢሆንና ለእርቅና ለወንድማማችነት ቅድሚያ ሰጥተን ቢሆን ኖሮ ዛሬ ላይ ስለሰላም እንጂ ስለጦርነት የምናወራ ባልሆንን ነበር። በጊዜ ያልተደፈኑ ትንንሽ ክፍተቶች መቼም የማይጠራ ክፉ ታሪክ የሚወለድባቸው ማህጸኖች ናቸው። ቀዳዳዎቻችን ተደፍነው ቢሆንና ነገን አርቆ በሚያይ ልበ ብርሀን ስልሳሌ ስር የቆምን ቢሆን ኖሮ ይሄን ሁሉ የጦርነት ዋጋ ባልከፈልን ነበር።

ሀገር አቅኙ ምክረ ሀሳቦች በእኔ እበልጥ እኔ ሽኩቻ ውስጥ ሳይሆን በሚዛናዊነት ውስጥ የተቃኙ፣ ነገን ዛሬ በሚሰራ የፖለቲካ እሳቤ እንዲሁም ጦርነትን በሚሽር ሰላም አምጪ የጋራ እሴት ላይ ጥናት የሚያደርግ በውጤቱም ሀገር የሚጠቅም የበጎ ትውልድ መብቀያ ነው። ጠማማውን አቅንቶ፣ ወልጋዳውን ገርቶ የሰላም መንገድ የሚሰጥ አስተሳሰብ ነው። እንዲህ አይነቱ አዲስ ምልከታ ትላንት ላይ ተንጸባርቆ ቢሆን ዛሬ ላይ ስለሰላም የምንጽፍ፣ ስለኢትዮጵያዊነት የምንናገር እንሆን ነበር።

በየትም ይምጣ ከማንጋርም ይሁን ጦርነት በበጎ የሚነሳ ገጽ የለውም። ለዚህ ደግሞ ያለፉና የቅርብ ጊዜ ታሪኮቻችንን ማስታወስ ይቻላል። በነውራቸው አቻ የሌላቸው ትላልቅ የጥላቻ ቁርሾዎች የሚፈጠሩት ጦርነት ውስጥ ነው። ለጊዜው ያሸነፍን ይመስለናል እንጂ ዛሬ ነገ ሲሆን በብዙ ዋጋ የሚያስከፍል ሆኖ የሚመጣ ነው። በዓለም ላይ ያሉ በጦርነት የተሳተፉና ዋጋ የከፈሉ ሀገራት ወደ ኋላ ሄደው አንድና ሁለት ነገሮችን እንዲያስተካክሉ እድል ቢሰጣቸው ብዙዎች በማወቅና ባለማወቅ የገቡበትን የጦርነት ታሪክ በሰላም መቀየር የሚመኙ ሆነው ይገኙ ነበር።

የእኛን ሀገር የጦርነት ታሪክ ከሌላው ሀገር ለየት የሚያደርገው ካለፈው አለመማራችን ነው። በጣም ከሚደንቀኝ የፖለቲካ ጨዋታ መሀል አንዱ ካለፈው ተምሮ መጪውን የተሻለ ለማድረግ ጥረት አለመኖሩ ነው። ከጦርነት ወደጦርነት መገላበጥ እጅግ አሳፋሪ ድርጊት ከመሆኑም በተጨማሪ ለግዙፍ አገርና ለባለታሪክ ሕዝብ የማይመጥን እንዲሁም በትውልድ ነገ ላይ መቀለድ ጭምር ሆኖ የሚታይ አሳፋሪ ድርጊት ነው።

በሀሳብ በልጽጎ ሰላማዊ መሆን ይቻላል እኮ። በሰላም ጎልምሶ ሰላማዊ የመሆን የጥንት ልማድ አለን እኮ። በሰላም ስለሰላም መወያየት ለምን አቃተን? አትጠራጠሩ ያቃተን በሀሳብ መበልጸግ፣ በሀሳብ መራመድ ነው። በሀገር ጉዳይ ላይ ስለሰላም በምክክር ያልነቃ ትውልድ የመፍጠራችን ነገር በፖለቲካው ምህዳር ዙሪያ የሚነሳ ትልቁ ነውራችን ነው። ኢትዮጵያ ከቃል ይልቅ በተግባር የምትገለጽ የድርጊት ውጤት እንጂ አጋጣሚ ስናገኝ በጥሩ ቃላት ፍቅራችንን በመግለጽ የምታበቃ አይደለችም።

እስኪ ወደጦርነት የሚወስዱ የከሸፉና ያረጁ አመለካከቶችን እንተውና ሰላም አምጪ በሆኑ አመለካከቶች ላይ እንቁም። በዓለም ላይ ጦርነት ያልነካቸው ቢነካቸው እንኳን ከአንድ ጊዜ ጥፋታቸው ተምረው ጦርነት በቃኝ ያሉ ሀገራት ሞልተዋል። ለአብነት ሕንድን መውሰድ ይቻላል። ሕንድ ላለፉት ሁለት መቶ ዓመታት በማንም ላይ ጦርነት ከፍታ ማንም ጦርነት ከፍቶባት አያውቅም። ካናዳ፣ አይስላንድ፣ ኒውዝላንድ በሰላማዊነታቸው የሚታወቁ ጦርነት ጠል ሀገራት ናቸው። ሌሎችም በርካታ ሀገራት አሉ ከአውዳሚና አትራፊ ካልሆነ ጥፋታቸው ተምረው ጤነኛና ሰላማዊ ትውልድ መፍጠር ላይ ያተኮሩ።

ብልህ የብልህት ስሙን ያገኘው ቀድሞ በመንቃት ከሌሎች ጥፋት ስለተማረ ነው። ሞኝ የሞኝነት አስጻያፊ ስያሜውን ያገኘው ከሌሎች አይደለም ከራሱ መማር ስላልቻለ ነው። አንዳንዶች ቀድመው በመንቃት ከሌሎች ጥፋት ተምረው ራሳቸውን ከጥፋት ይታደጋሉ። ሌሎች ከራሳቸው መማር ሳይችሉ በተደጋጋሚ መተላለፍ የማያባራ ሰቆቃን ያደምጣሉ። እኛም እንደሀገር፣ እንደመንግስት፣ እንደዜጋ፣ እንደፖለቲከኛ ከሞኝነት ወደብልህነት የሚያሻግረንን የሀሳብ ልዕልና መውረስ ትላንትን ላለመድገም የመጨረሻ ዋስትናችን ሆኖ የሚጠቀስ ነው።

በአክሳሪ ጦርነት ትላንት የሚቆጨው ትውልድ ያስፈልገናል። አዋራጅ ከሆነ የኃይል አሰላለፍ ወጥተን ስለአንድነት በአንድነት የምንቆምበት የወንድማማችነት ሕብረት በእጅጉ ግድ የሚለን ጊዜ ላይ ነን። በጦርነት ፍልስፍና አንድ ሰው ሲሞት ሀገር እየተሸረፈች ነው። የእርስ በርስ ትንቅንቅ ሲሆን ደግሞ ከዚህም የባሰ ትርጉም ያለው ነው። በእውነቱ ሰላም እንደኛ የናፈቀው ባለመኖሩ አምናለው። ከጦርነት ወደጦርነት በሆነ መገላበጥ ብዙ ዘመንን በከንቱ አሳልፈናል። ከሰላም ወደሰላም የሽግግት ፖለቲካ እንደናፈቀን ስድስት አስርት ዓመታት ጠቡ።

ሀገር አቅኚ ምክረ ሀሳቦች ከእንዲህ አይነት መጠፋፋት የሚታደጉን፣ የጠፋን በካሳ፣ ያዘነን በይቅርታ አሽረው፣ ወደ አንድነት የሚመልሱን የድሮነት አዋጆች ናቸው ብል አላጋነንኩም። ለማይጠቅመን ስንዳክር በብዙ ወደኋላ ቀርተናል። ይሄ ሊያስቆጨን ሲችል ነው ለሀገር አቅኚ ምክረ ሀሳቦች የምንገዛው። ተመልሰን እዛው ከሆንን ከነውሮቻችን መራቅ አስቸጋሪ ነው የሚሆንብን።

ችግሮቻችን ከእኛው ጋር የመሰንበታቸው፣ በአንድ ችግር ሁለት ሶስት ጊዜ ዋጋ የመክፈላችን ምክንያት ሲጠና የምናገኘው ከሀገር አቅኚ ምክረ ሀሳብ ይልቅ በትርኪምርኪ ጉዳይ ላይ ማተኮራችን እንደሆነ የሚያጠራጥር አይደለም። ችግሮቻችን ማንም ያልጠነሰሳቸው እኛው አምጠን የወለድናቸው፣ በእኛው እሽሩሩ የጎለመሱ እኛኑ መልሰው እያጠቁን ያሉ ናቸው። ይሄን ተረድተን ለዳግም ጥፋት እድል ሳንሰጥ በተውጣጣ የሀሳብ መዋጮ ለተሀድሶ እንቁም።

> **ችግሮቻችን ከእኛው ጋር የመሰንበታቸው፣ በአንድ ችግር ሁለት ሶስት ጊዜ ዋጋ የመክፈላችን ምክንያት ሲጠና የምናገኘው ከሀገር አቅኚ ምክረ ሀሳብ ይልቅ በትርኪምርኪ ጉዳይ ላይ ማተኮራችን እንደሆነ የሚያጠራጥር አይደለም። ችግሮቻችን ማንም ያልጠነሰሳቸው እኛው አምጠን የወለድናቸው፣ በእኛው እሽሩሩ የጎለመሱ እኛኑ መልሰው እያጠቁን ያሉ ናቸው። ይሄን ተረድተን ለዳግም ጥፋት እድል ሳንሰጥ በተውጣጣ የሀሳብ መዋጮ ለተሀድሶ እንቁም**

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## የሳይበር ደህንነት ንቃተ ሕሊናን የማጎልበቻው ወር

**ወርቅነሽ ደምሰው**

በዓለም በተለያዩ ዘርፎች ለሚከናወኑ ተግባሮች ፍቱን ቴክኖሎጂ እየሆነ የሚገኘው የዲጂታል ቴክኖሎጂ፣ የምርት እድገት፣ የግንኙነት መሳለጥ፣ የደህንነትና የመሳሰሉት ጉዳዮች ሲታሰቡ ቀዳሚው ተጠቃሽ ቴክኖሎጂ መሆን ችሏል፤ ዓለም አንድ መንደር ሆናለች ሲባልም ቴክኖሎጂው ይዞት የመጣው ሰፊ እድል ነው።

ግብይት፣ የገንዘብ ዝውውር እየተሳለጠ፣ የትምህርቱ፣ የጤናው፣ ወዘተ ዘርፎች ስራም በርቀት ጭምር እየተፈጸመ ነው። ግብርናው፣ ደህንነቱ፣ መከላከያው፣ ወዘተ ያለዲጂታል ቴክኖሎጂ ብዙ ሊቀላጠፍ ውጤታማ ሊሆን የማይችልበት ደረጃ ላይ ደርሷል። ቴክኖሎጂውን መጠቀም አማራጭ ሳይሆን የግድ እስከመሆን ደርሷል።

ይህ ቴክኖሎጂ በአግባቡ ጥቅም ላይ ካልዋለ፣ ተገቢው ጥበቃ ካልተደረገለት ሊያስከትል የሚችለው ጉዳትም የዚያኑ ያህል መሆኑ እየተጠቆመ ይገኛል። በሳይበር ጥቃቶች የተነሳ ከፍተኛ ጉዳቶች እየደረሱ ናቸው፤ ሊደርሱ ይችላሉ የሚሉ ስጋቶችም ብዙ ናቸው። የሳይበር ጥቃትን ለመከላከል በሚደረጉ ጥረቶች ብዙዎቹ ሊደርሱ ይችላሉ የተባሉ ጉዳቶችን ከመድረሳቸው በፊት እንዲመክኑ እየተደረገ እንጂ ጉዳቱ አስከፊ ሊሆን እንደሚችል መረጃዎች ይጠቁማሉ።

የዓለም ኢኮኖሚክ ፎረም መረጃ እንደሚያመላክተው፤ በቀጣይ አስር ዓመታት በዓለም ላይ ከሚከሰቱ ከፍተኛ አደጋዎች መካከል ከአየር ብክለት፣ ከሀሰተኛ መረጃ ስርጭት፣ ከአክራሪነትና ከኑሮ ውድነት በመቀጠል በአምስተኛ ደረጃ የዓለማችን ስጋት ተብሎ የተቀመጠው የሳይበር ጥቃት ሆኗል። የሳይበር ጥቃት ባሕሪው አለማቀፍና ድንበር የለሽ በመሆኑ የዓለም አገራት ሁሉ ስጋት እንደሆነ ቀጥሏል።

የሳይበር ደህንነት ስጋት እየጨመረ መምጣቱን ተከትሎ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሳይበር ጥቃቶች የሚያስከትሉት ኪሳራ ተበራክቷል። በዓለም አቀፍ ደረጃ በሳይበር ጥቃት እ.ኤ.አ በ2022 የስምንት ነጥብ 44 ትሪሊዮን ዶላር ኪሳራ ደርሷል፤ እ.ኤ.አ በ2027 በዚሁ ጥቃት ሊደርስ የሚችለው ጥቃት ከፍተኛ መሆኑ እየተገለጸ ነው፤ በዚህ ጥቃት ብቻ ሊደርስ የሚችለው ኪሳራ ወደ 23 ነጥብ 84 ትሪሊዮን ዶላር ይሆናል ተብሎ ተገምቷል።

ኢትዮጵያም ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ የሳይበር ጥቃት ተጋላጭነቷ እየሰፋና እየጨመረ መጥቷል። በኢትዮጵያ የተከሰቱ የሳይበር ጥቃት ሙከራዎችን ስንመለከትም በ2015 ዓ.ም ስድስት ሺ 959 የሳይበር ጥቃት ሙከራዎች የደረሱ ሲሆን፤ ይህ አሃዝ በ2016 ዓ.ም ወደ ስምንት ሺ854 ከፍ ብሏል። ከነዚህም ውስጥ ከፍተኛው ድርሻ የሚይዙት በቁልፍ መሰረተ ልማቶች ላይ የተሞከሩ ጥቃቶች ናቸው።

ሳይበር ጥቃት እየጨመረ መምጣቱ ደግሞ አገራት ራሳቸውን መከላከል እንዳለባቸውና የዜጎቻቸውና የተቋሞቻቸው የሳይበር ደህንነት ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግን የሚጠይቅ ነው። በዚህም የተነሳ ‹‹የሳይበር ደህንነት›› ወር በዓለም አቀፍ ደረጃ በጥቅምት ወር እንዲካሄድ ውሳኔ ላይ ተደርሶ በየዓመቱ እየተካሄደ ይገኛል።

‹‹የሳይበር ደህንነት›› ወር በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ21ኛ ጊዜ በኢትዮጵያ ደግሞ ለአምስተኛ ጊዜ በመከበር ላይ ይገኛል። በአትዮጵያም በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር አዘጋጅነት በሀገር አቀፍ ደረጃ ላለፉት አራት ዓመታት የሳይበር ደህንነት ወር ሲካሄድ ቆይቷል። ዘንድሮም ለአምስተኛ ጊዜ ‹‹የቁልፍ መሰረተ-ልማት ደህንነት ለዲጂታል ሉዓላዊነት›› በሚል በመሪ ሀሳብ እየተከበረ ይገኛል።

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ዋና ዳይሬክተር ትዕግስት ሀሚድ እንዳሉት፤ የዘንድሮው የሳይበር ደህንነት ወር ዋነኛ ትኩረት የሀገሪቱን ቁልፍ መሰረተ ልማቶች እና ተቋማት የሳይበር ደህንነት በመጠበቅ የሳይበር ሉዓላዊነትን ማረጋገጥ ላይ ትኩረት ያደረገ ነው። ከዚህ አኳያ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር የሳይበር ጥቃትን በመከላከል ረገድ የነቃ የሰው ልጅ ሚና ከፍተኛውን ቦታ የሚይዝ በመሆኑ የዜጎችን ብሎም የተቋማትን የሳይበር ደህንነት ንቃተ ሕሊና ለማጎልበት የሚያስችሉ ፕሮግራሞችን ቀርጾ በመስራት ላይ ይገኛል።

ቁልፍ መሰረተ ልማት ለአንድ ሀገር ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ እድገት ያለው ፋይዳ ከፍተኛ ነው የሚሉት ዋና ዳይሬክተሯ፤ የጠቀሜታውን ያህል ደግሞ ጥቃት በሚደርስባቸው ጊዜ በዜጎች የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ እንዲሁም በሀገር ብሔራዊ ጥቅም እና ደህንነት ላይ የሚያስከትሉት ጉዳት ከፍተኛ በመሆኑ ልዩና ጠንካራ ጥበቃ ሊደረግላቸው እንደሚገባ ይገልጻሉ።

**በሁሉም የኅብረተሰብ እርከኖች ግንዛቤን ማሳደግ ሀገራዊ የሳይበር ደህንነት ደረጃን ለማሻሻል በጣም ውጤታማ ከሆኑ መንገዶች አንዱ ነው። በትምህርታዊ ዘመቻዎች፣ በማኅበረሰብ ተሳትፎ እና በስልጠና ተነሳሽነት ዜጎች የኢትዮጵያን ዲጂታል ሉዓላዊነት በማረጋገጥ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማብቃት ይገባል**

በአገሪቱ ነባራዊ ሁኔታም ለዲጂታላይዜሽን ሽግግር የተሰጠውን ከፍተኛ ትኩረት ተከትሎ በርካታ የመንግሥትም ይሁኑ የግል ተቋማት አገልግሎታቸውን ፈጣን፣ ቀልጣፋና ተደራሽ በሆነ መልኩ ለመስጠት አስችሏል የሚሉት ዋና ዳይሬክተሯ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በቁልፍ መሰረተ ልማቶች እና መሰረተ ልማቶቹ በሚይዟቸው መጠነ ሰፊ መረጃዎችና ዳታዎች ላይ የሚደርሱ የሳይበር ደህንነት ተጋላጭነቶችና ስጋቶችም እንዲሁ ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመሩ መምጣታቸውን ተናግረዋል።

እሳቸው እንዳብራሩት፤ በአንድ ተቋም ላይ የሚደርሰው የሳይበር ጥቃት ሌሎቹንም የአገልግሎት መስጫ ተቋማት ሊያቋርጥ፣ ሊያስተጓጉል ወይም ሙሉ በሙሉ ሊያወድም ይችላል። ቴክኖሎጂው የጠቀሜታውን ያህል ጥቃት በሚደርስበት ጊዜ ከፍተኛ ውድመትና ኪሳራ ያስከትላል። ከዚህ ቀደም በሀገሪቱ ቁልፍ መሰረተ ልማቶች ስለሚለዩበት ሁኔታ፣ ስለሳይበር ደህንነት ፕሮግራምና የደህንነት ማሕቀፎች፣ ስለተቋማት ኃላፊነትና የአስገዳጅ ሕግ ወይም ቁጥጥር በሚመለከት የሕግ ማሕቀፍ አለመኖሩ ሀገራዊ የሳይበር ደህንነትን በተሟላ መልኩ ለማረጋገጥ የሚደረገው ጥረት ውጤታማ እንዳይሆን በማድረግ ተግዳሮት ሆኖ ቆይቷል።

ይህንንም መነሻ በማድረግ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር በአዋጅ በተሰጠው ስልጣን መሰረት በሀገሪቱ የቁልፍ መሰረተ ልማቶችን የሳይበር ደህንነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ረቂቅ አዋጅ በማዘጋጀትና በየደረጃ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ሰፊ ውይይት በማድረግ አጸድቆ ለማውጣት ለሚመለከተው አካል ተልኳል። ረቂቅ አዋጁ በዋናነት በሀገሪቱ ቁልፍ መሰረተ ልማቶችን ለመለየትና ልዩ ጥበቃ ለማድረግ ወሳኝ ሚናን ከመጫወቱም ባሻገር የሀገሪቱን ዲጂታላይዜሽን ኢኒሼቲቮች ደህንነት በማረጋገጥ የሀገርን ደህንነትና የዜጎችን ተጠቃሚነት ለማስጠበቅ ጉልህ አስተዋፅዖ ይኖረዋል።

አስተዳደሩ ከሕግ ማዕቀፉ ባሻገር ሀገራዊ ቴክኖሎጂ በማረጋገጥ እንዲሁም የዘርፉን ደህንነት ለማስጠበቅ የሚያስችል የሰው ኃይል በማልማት ረገድ የተለያዩ ሥራዎች በመስራት ላይ ይገኛል የሚሉት ዳይሬክተሯ፤ በዚህም በሀገሪቱ ቁልፍ መሰረተ-ልማቶች እና እነዚህን የሚያስተዳደሩ ተቋማት የሳይበር ደህንነት መረጋገጥ ለሀገራዊ የዲጂታል ሉዓላዊነት መረጋገጥ ያለውን አበርክቶ በማሳየት በቀጣይ ለሚሰሩ ስራዎች መደላድል ለመፍጠር እንዲሁም ቀጣይ አቅጣጫዎች የሚመላከቱበት መሆኑን አስረድተዋል።

የብሔራዊ ባንክ ገዥ አቶ ማሞ ምህረቱ በበኩላቸው ዓለም ወደ ዲጂታል ትራንስፎርሜሽን በገባችበት በዚህ ጊዜ ከሳይበር ደህንነት ርእሰ ጉዳይ ውጪ ወቅታዊ እና ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ሌላ አብይ ጉዳይ ሊኖር አይችልም ይላሉ። እሳቸው እንደሚሉት፤ ቁልፍ መሠረተ ልማት ከማንኛውም ዘመናዊ ማኅበረሰብ መሰረታዊ ጉዳዮች መካከል ቀዳሚው ነው። የእነዚህን መሰረተ ልማቶች ደህንነታቸውን ማረጋገጥ ባለንበት የዲጂታል ዘመን ሀገራዊ ሉዓላዊነታችንን ለመጠበቅ ወሳኝ ነው።

ስለ ዲጂታል ሉዓላዊነት ሲነሳ፣ አንድ ሀገር በዲጂታል ንብረቶቿ፣ ስርዓቶቿ እና ዳታዎቿ ላይ የመቆጣጠር ችሎታና አቅሙን ማዳበር እንዳለበት ጠቅሰው፣ ኢትዮጵያም የዲጂታል ሀብቶቿን የመከላከል እና የመጠበቅ፣ ነፃ የቴክኖሎጂ ውሳኔዎችን የመወሰን እና የዜጎቿን ደህንነት እና ግላዊነት የማረጋገጥ አቅም ሊኖራት ይገባል ብለዋል። የሀገሪቱ ወሳኝ መሠረተ ልማቶች ማለትም የቴሌኮሙዩኒኬሽን፣ የኢነርጂ፣ የፋይናንስ ሥርዓቶች፣ መጓጓዣ እና የጤና አጠባበቅ የመሳሰሉ ከዲጂታል ቴክኖሎጂዎች ጋር በጥልቅ የተቆራኙ ናቸው። እነዚህ መሰረተ ልማቶች ሁሉን አቀፍ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነትና የጂኦፖለቲካል ተጽዕኖ ለመፍጠር መሰረቶች ናቸው ሲሉ ገልጸዋል።

እንደ ሀገር የዲጂታል መሠረተ ልማታችንን ስንገነባ እና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ከወሳኝ ስርዓታቸው ጋር ስናዋህድ፣ የግድ በንቃትና በጥንቃቄ ሊከወን ይገባል የሚሉት አቶ ማሞ፤ የኃይል ማከፋፈያዎች፣ የባንክ ስርዓቶች፣ የትራንስፖርት መሰረተ ልማቶች ወይም የጤና አጠባበቅ ኔትወርኮች ላይ አንድ ጊዜ ጥቃት ከደረሰ በማህበረሰባችን ላይ ከፍተኛ መዘዝ ሊያስከትል እንደሚችል አስገንዝበዋል።

ይህ ስጋት ቴክኒካል ስጋት ብቻ ሳይሆን ጂኦፖለቲካዊ አንድምታ ያለው መሆኑን ጭምር ጠቅሰው፤ የሳይበር ጥቃቶች የብሔራዊ ደኅንነትን ለአደጋ የማጋለጥ፣ ሕዝቡ በመንግሥት ላይ ያለውን አመኔታ የማሳጣት እና ሀገሪቱ በዓለም አቀፍ መድረክ ባላት ቁመና ላይ ተጽዕኖ የመፍጠር አቅም እንዳለው ያብራራሉ።

‹‹ዲጂታል ሉዓላዊነትን ለማስጠበቅ የሳይበር ደህንነት ከሀገራዊ አጀንዳችን መካከል ግንባር ቀደም መሆን አለበት። የሀገራችንን ወሳኝ መሠረተ ልማቶችን ከጥቃት ለመጠበቅ ጠንካራ የፖሊሲና የሕግ ማሕቀፎችን፣ ሀገራዊ የቴክኖሎጂ ባለቤትነትን፣ በዘርፉ ብቁና ዓለማቀፍ ተወዳዳሪ የሆነ የሰው ኃይል ማልማት በእጅጉ ይጠይቃል›› ሲሉም አስታውቀዋል።

ከዚህ አኳያ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር የሀገሪቱን የሳይበር ደህንነትና ሉዓላዊነት የማስጠበቅ ኃላፊነት እንደተሰጠው ተቋም፤ ዘርፉ የሚመራበትን የሕግ ማሕቀፎችን ከማውጣት፣ ሀገራዊ የእውቀትና የቴክኖሎጂ ባለቤትነትን በማረጋገጥ፣ እንዲሁም በዘርፉ ብቁ የሆነ የሰው ኃይልና አመራር በማፍራት ረገድ ተጨባጭ ሥራዎችን መስራቱን አስታውቀዋል።

እሳቸው እንዳብራሩት፤ የሳይበር ደህንነት ከማረጋገጥ አኳያ የመንግስት እና የግሉ ዘርፍ አጋርነት ወሳኝ ሚናን ይጫወታሉ። የግሉ ሴክተር ከሀገራዊ ደህንነት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን እንደ ቴሌኮሙኒኬሽን፣ ፋይናንሺያል እና ኢነርጂ ያሉ በርካታ ስርዓቶችን በባለቤትነት ያስተዳድራል። የሳይበር ስጋቶችን ለመከላከል አንድ ወጥ የሆነ መከላከያ አማራጮችን ለመተግበር በመንግሥት እና በኢንዱስትሪ መካከል ያለው ትብብር አስፈላጊ ነው። አንድ ላይ መረጃን መጋራት፣ ውስን የሆነውን የሕዝብ ሃብት በጋራ በመጠቀምና በትብብር በመስራት ሊከሰቱ የሚችሉ የሳይበር ጥቃት አደጋዎች ፈጣን ምላሽ መስጠት ያስችላል።

ይህ የሳይበር ደህንነት የግንዛቤ ማስጨበጫ ወር የሳይበር ደህንነት የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ወይም በየተቋማቱ ያሉ የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ባለሙያዎች ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የሁላችንንም-የጋራ ኃላፊነት መሆኑን የሚያስታውስ ሁነት ብለዋል።

ወሳኝ መሠረተ ልማቶችን ለመጠበቅ እያንዳንዱ የመንግሥት ተቋም፣ የንግድ ድርጅት እና ግለሰብ በዚህ ላይ ሚና አላቸው። በሁሉም የሕብረተሰብ እርከኖች ግንዛቤን ማሳደግ ሀገራዊ የሳይበር ደህንነት ደረጃን ለማሻሻል በጣም ውጤታማ ከሆኑ መንገዶች አንዱ ነው። በትምህርታዊ ዘመቻዎች፣ በማኅበረሰብ ተሳትፎ እና በስልጠና ተነሳሽነት ዜጎቻችን የኢትዮጵያን ዲጂታል ሉዓላዊነት በማረጋገጥ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማብቃት ይገባናል ሲሉ አስገንዝበዋል።

በተለይም የመገናኛ ብዙሃን የማኅበረሰቡን የሳይበር ደህንነት ንቃተ ሕሊና ግንዛቤ ከፍ የሚያደርጉ አስተማሪ ፕሮግራሞችን በመቅረጽ የበኩላቸውን ሚና ሊወጡ ይገባል ያሉት አቶ ማሞ፤ ‹‹አምስተኛውን የሳይበር ደህንነት ግንዛቤ ማስጨበጫ ወርን ስናከብር ምን ያህል ርቀት እንደሄድን ነገር ግን ምን ያህል መሄድ እንዳለብን እናስብ ሲሉም አስታውቀዋል። የሀገሪቱን ወሳኝ መሠረተ-ልማቶች ከጥቃት መጠበቅ የሳይበር ጥቃቶችን መከላከል ብቻ ሳይሆን የሀገሪቱን የወደፊት እጣ ፈንታ መጠበቅ መሆኑን ጠቅሰው፣ ‹‹ኢትዮጵያ በዲጂታል ዘመን ሉዓላዊ፣ ነጻ እና ጠንካራ ሆና እንድትቀጥል ማድረግ ነው›› ይላሉ።

የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች፣ የቁልፍ ተቋማት የሥራ ኃላፊዎች፣ የንግድ ተቋማት የስራ ኃላፊዎች፣ በሳይበር ደህንነትና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ (አይቲ) ዘርፍ የተሰማሩ አካላት እንዲሁም ሁሉም ዜጋ ለወሳኙ መሠረተ ልማት ደህንነት መጠበቅ በሚያስችሉ ተግባራት ላይ ትኩረት እንዲያከናውኑም አቶ ማሞ አሳሰበዋል። ‹‹በጋራ፣ አስተማማኝ፣ ሉዓላዊት ዲጂታል ኢትዮጵያን መገንባት የምንችለው በጋራ ተቀናጅተን መስራት ስንችል ነው›› ሲሉም ተናግረዋል።

# ወቅታዊ ትንታኔ

# በኢትዮ ቴሌኮም የድርሻ ሽያጭ ሀገር እና ሕዝብ ምን ያህል ይጠቀማሉ ?

**አመለወርቅ ከበደ**

ኢትዮጵያ በመንግስት ይዞታ ስር ያሉ ድርጅቶችን የተወሰነ ድርሻ ወደ ሕዝብ ለማስተላለፍ እንቅስቃሴ ጀምራለች። እንቅስቃሴውም በኢትዮ ቴሌኮም ተጀምሯል። ባለፈው ሳምንትም ኢትዮ ቴሌኮም 10 በመቶውን ድርሻ ለሕዝብ ማቅረቡን የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ይፋ አድርገዋል።

በወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንደተናገሩት፤ ኢትዮ ቴሌኮም ረጅም ዓመታትን ያስቆጠረ ኩባንያ ነው። በተቃራኒው ሳፋሪኮም የቅርብ ዓመታት ታሪክ ነው ያለው። ነገር ግን ሳፋሪኮም የብዙ ባለሀብቶችና ስራ ፈጣሪዎች ኩባንያ ስለሆነ ኬኒያ ሳይበቃው ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ለማልማት ችሏል።

እድሜ ጠገቡ ኢትዮ ቴሌኮም ብዞዎችን የማሳተፍ ልምምድ መፍጠር ባለመቻሉ፤ ከኢትዮጵያ አልፎ ጎረቤት ሀገራት ላይ መስራት አልቻለም። ስለዚህ የድርሻ ገበያ መጀመር ሌሎች ሀገራት በመሄድ ከገበያው ጋር የመሻማት፣ የመስጠት እና የመቀበል ዕድል ያገኛል። የኢትዮ ቴሌኮም የድርሻ ገበያ መጀመር ለበርካታ ኢትዮጵያውያን የምስራች እንደሚሆንም ገልጸዋል።

የኢትዮ ቴሌኮም ዋና ስራ አስፈጻሚ ፍሬሕይወት ታምሩ በበኩላቸው አጠቃላይ የኩባንያው ድርሻ መቶ ቢሊዮን ብር ነው። ከዛ ውስጥ 10 በመቶው ነው ለኢትዮጵያውያን የቀረበው የባለቤትነት ድርሻ። ይህም 100 ሚሊዮን ድርሻ ሲሆን አንዱ በ300 ብር ሲሸጥ አጠቃላይ የቀረበው ድርሻ የ30 ቢሊዮን ብር ዋጋ እንዳለው ነው የገለጹት።

ዛሬ የዝግጅት ክፍላችን ኢትዮ ቴሌኮም ለገበያ ያቀረበው 10 በመቶው ድርሻ ለሕዝብ እና ለመንግስት ያለው ፋይዳ ምንድነው በሚለው ዙርያ የኢኮኖሚ ባለሙያዎችን አነጋግሯል።

የኢኮኖሚ ባለሙያ የሆኑት ዳዊት ተሻለ (ዶ/ር) እንደተናገሩት፤ ኢትዮ ቴሌኮም መንግስት በወሰነው መሰረት 10 በመቶውን ድርሻ ለሕዝብ እሸጣለው ሲል ኩባንያውን ወደ ግል ዘርፍ በማዞር ሂደት ውስጥ የባለቤትነት ድርሻውን ለሕዝብ ማካፈል ማለት ነው።

በአብዛኛው እንደ ባንክ እና ቴሌኮም ያሉ ዘርፎች ከደህንነትም አንጻር ለረጅም ግዜ መንግስት ይዞት የቆየው ነው። ግን አሁን በተጀመረው መንገድ የባንክ ዘርፉ ለውጮች ክፍት እያደረገ ነው። እንደዚሁም የቴሌኮሙን መጀመሪያ ለሀገር ውስጥ እድሉን ሰጥቶ በመቀጠል ወደ ሌሎች እንደሚሄድ ጅማሮውን ለማሳየት ነው 10 በመቶ ጅርሻ እድል የሰጠው ።

ይህ እንደመግስት ተቋም አዲስ ባይሆንም፤ በቴክኖሎጂው ዘርፍ የመጀመሪያው ጅማሬ ነው የሚሉት ዳዊት (ዶ/ር)፤ በዚህም ለዜጋው አዲስ የገበያ እድል ተከፈተ ማለት ነው።

ባለሙያው እንደሚናገሩት የአክሲዮን ድርሻው መሸጡ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለሕዝቡ ጠቀሜታ አለው። የመጀመሪያ አንድ ግለሰብ 10 ሺህ ብር አካባቢ የሚጠጋ ገንዘብ አውጥቶ ዝቅተኛውን ድርሻ ሲገዛ የኔ የሚለው ኩባንያ ይኖረዋል ወይም ንብረት የማፍራት ዕድል ይፈጠርለታል።

በሌላ በኩል ደግሞ አዲስ የኢንቨስትመንት ወይም የንግድ አማራጭ እንደሚሰጥ በመግለጽ፤ በሀገር ደረጃ የተለመዱት የንግድ አማራጮች የሸቀጣ ሸቀጥ እቃዎችን መነገድ፤ ምርቶችን አምርቶ ለገበያ የማቅረብ እና ቤት ገንብቶ ከመሸጥ ውጭ አዳዲስ የገቢ አማራጮች መኖራቸውን ለሕዝብ ያስተዋውቃል። በአክሲዮን የመገበያየት ሂደትን ለሀገራችን ለማስዋወቅ ያግዛል።

ከዚህ ውስጥ ምን ያህል ሕብረተሰብ ይጠቀማል የሚለው ሲታይም፤ በተቀመጠው ከፍተኛ አክሲዮን የመግዛት ጣራ መሰረት ሁሉም ሰው የአንድ ሚሊዮን ብር አክሲዮን ቢገዛ 30 ሺህ ሰው ኢትዮ ቴሌኮም ውስጥ የባለቤትነት ድርሻ ይኖረዋል። የአንድ ሚሊዮን ብር መግዛቱ ቀርቶ ሁሉም ሰው የ100 ሺህ አክሲዮን መግዛት ቢችል፤ ኩባንያው 300 ሺህ የሚደርስ ዜጋ የባለቤትነት ድርሻ ይኖረዋል። የሚገዛበት ገንዘብ ዝቅ እያለ በመጣ ቁጥር የባለቤቶቹ ቁጥር ከፍ ይላል በማለት ያስረዳሉ።

ባለሙያው እንደሚያስረዱት፤ ከኩባንያው አንጻር ደግሞ ሲታይ በአክሲዮን ሽያጭ 30 ቢሊዮን ብር ወደ ኢኮኖሚው ያገባል። በሁለት መልኩ ሲታይ ለመንግስት ከሚያመነጨው ገቢ እና ለቴሌ እራሱን ከሚሰጠው ጥቅም አንጻር 30 ቢሊዮን ብር ቀላል አይደለም።

የገቢ ግብር መንግስት ገቢ የሚያገኝበት አንዱ መንገድ እንደመሆኑ በአክሲዮን ሺያጩ የሚገኘው የአገልግሎት ክፍያ እና 15 በመቶ ተጨማሪ እሴት ታክስ መንግስት ከፍተኛ ገቢ ያገኛል። ይህም መንግስትን ይደጉማል፤ የገቢ ምንጩንም ያሰፋል ይላሉ።

ከኩባንያው አንጻር ደግሞ በሚያገኘው ገቢ አገልግሎቱን በማዘመን እና በማስፋፋት ተወዳዳሪነቱን እንዲያሳድግ ያግዘዋል። እንደ ሳፋሪኮም አይነት ድርጅቶች እየመጡበት ስለሆነ ከአክሲዮን ሽያጭ በሚያገኘው ገቢ የአገልግሎት ጥራት ለማዘመን እና የቴሌኮም አገልግሎት በማስፋፋት ረገድ መሰረተ ልማቶችን ለማሟላት ያስችለዋል በማለት ይገልጻሉ።

ዳዊት (ዶ/ር) እንደሚገልጹት፤ ይህን ሽያጭ በማድረግ መንግስት እስከ 33 ቢሊዮን ብር የማግኘት እድል ስለሚኖረው፤ ትልቅ የገንዘብ አቅም ይፈጥርለታል። በሁለተኛ ደረጃ መንግስትም ገቢ በማግኘት ያቀዳቸውን የልማት ግቦች እንዲያሳካ ይረዳዋል። በረጅም ግዜ ደግሞ የግብር መሰረቶቹን ያሰፋለታል ።

የግሉ ዘርፍ ወደ ቴሌኮም መግባቱ ገቢ ከማግኘት አንጻር የውስጥ አሰራሩን ውጤታማ ያደርገዋል። ያሉትን ሀብቶች በተገቢው መንገድ በመጠቀም ኩባንያው ገቢው እንዲያድግ፣ ወጪው እንዲቀንስ በማድረግ፤ አዳዲስ እውቀቶችን ይዘው የሚመጡ የቦርድ አባላት፣ የአስተዳደር አካላት ሊኖሩ ይችላሉ ሲሉ ይናገራሉ።

ሌላው ኩባንያው እየተስፋፋ ሲመጣ ኢንቬስተሮችን የመሳብ አቅሙ እያደገ ይመጣል። የዲጂታል ኢኮኖሚ ግንባታንም ያስፋፋል ይላሉ። ሆኖም አክሲዮን በማስተዳደር ሂደት ውስጥ ችግር እንዳይፈጠር የሕግ ማእቀፉ የሰፋና የተደራጀ መሆን አለበት። እንደ ሀገር የካፒታል ገበያ አሰራር አዲስ እየገባበት ያለ እንደመሆኑ ከወዲሁ በቂ እውቀት በመሰብሰብ ተቋም ግንባታ ላይ በደንብ መስራት ያስፈልጋል፡ ይላሉ፡

የአክሲዮን ሽያጩ በቴሌ ብር እየተከናወነ እንደመሆኑ፤ በሺዎች ዘንድ የጥቅም ግጭት እንዳይፈጠር፣ የአክሲዮን ሽያጩ 30 ቢሊዮን ብር ሲደርስ ቶሎ ብሎ ሽያጩን መዝጋት እንደሚያስፈልግ በመግለጽ፤ በቀጣይ ሼሮችን በማስፋት የውጭ ምንዛሬ ማግኛ መንገድ መታሰብ አለበት። ሌላው ከሽያጭ የሚገኘው ገንዘብ ለሕብረተሰቡ አንገብጋቢ በሆነ ጉዳይ ሊውል እንደሚገባም ሀሳባቸውን ያስቀምጣሉ።

በፖሊሲ ጥናት ኢንስትቲዩት ተመራማሪ እና የኢኮኖሚ ባለሙያ ጀማል ሞሀመድ (ዶ/ር) በበኩላቸው እንደሚገልጹት፤ 10 በመቶ ድርሻ ማለት የኩባንያው አጠቃላይ ሀብቱ እና ትርፍ ተደምሮ ዓለም አቀፍ ገማቾች ባስቀመጡት መሰረት የኢትዮ ቴሌኮም አጠቃላይ ዋጋ 100 ቢሊዮን ብር ነው በሚል ሃሳብ ይጀምራሉ ።

የ100 ቢሊዮን 10 በመቶ ደግሞ 10 ቢሊዮን ብር ነው። ስለዚህ አሁን ኩባንያው 10 ቢሊዮን ብሩን ወደ አክሲዮን ቀይሮ እየሸጠ ነው። 10 በመቶ ድርሻ የሚለው ነገር በአጭሩ ይህን ነው የሚያመለክተው ይላሉ።

አክሲዮኑ የቀረበበት ዋጋ የተጋነነ ነው የሚሉት ባለሙያው፤ የ10 ቢሊዮን ብር ሼር አቅርበው 30 ቢሊዮን ብር ነው ለማግኘት የታቀደው። አንድ የአክሲዮን ድርሻ የ100 ብር ዋጋ ነው ያለው። ነገር ግን የቀረበው በ300 ብር ነው። በዚህም አክሲዮኑ ያለው ዋጋ እና ገበያ ላይ የቀረበው ዋጋ በሁለት እጥፍ የጨመረ መሆኑን ያስረዳሉ።

ጀማል (ዶ/ር) እንደሚናገሩት፤ ባለፈው ዓመት ኩባንያው ያተረፈው ከ20 ቢሊዮን ብር በላይ ነው። በዚህ መሰረት ትርፉ 20 በመቶ ማለት ነው። ነገር ግን ሁለት እጥፍ የገበያ ዋጋ ተጨምሮበት ሲሸጥ ስድስት በመቶ ማለት ነው።

አንድ ሰው ብሩን ባንክ ቤት ቢያስቀምጥ ሰባት በመቶ ወለድ ያገኛል። ድርሻው የቀረበበት ዋጋ የተጋነነ ነው። ከኢኮኖሚክስ አንጻር ስድስት በመቶ እና ከዛ በታች ትርፍ የሚያስገኝ ከሆነ ገንዘቡ ባንክ ቤት ቢቀመጥ ሰባት በመቶ ትርፍ ስለሚያስገኝ የቴሌ የአክሲዮን ሽያጭ ከዚህ አንጻር ጥያቄ የሚነሳበት መሆኑን ያስረዳሉ።

ባለሙያው እንደሚያስረዱት፤ 10 በመቶ ድርሻ 100 ሚሊዮን ድርሻ ከሆነ ኢትዮ ቴሌኮም አጠቃላይ የኩባንያውን ድርሻ አንድ ቢሊዮን ድርሻ ማለት ነው። አንድ ቢሊዮን የአክሲዮን ድርሻ ከሆነ አጠቃላይ የካምፓኒው ዋጋ ለድርሻው ይካፈላል። 100 ድርሻም ከሆነ አጠቃላይ የካምፓኒው ዋጋ ለሼሩ ይካፈላል።

**የአክሲዮን ድርሻው መሸጡ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለሕዝቡ ጠቀሜታ አለው። የመጀመሪያ አንድ ግለሰብ 10 ሺህ ብር አካባቢ የሚጠጋ ገንዘብ አውጥቶ ዝቅተኛውን ድርሻ ሲገዛ የኔ የሚለው ኩባኒንያ ይኖረዋል ወይም ንብረት የማፍራት ዕድል ይፈጠርለታል**

አክሲዮኑ በ100 ብር ወይም በአንድ ሺህ ብር መቅረቡ ሳይሆን ተጽኖ የሚያደርገው አጠቃላይ የካምፓኒው ዋጋ ምን ያህል ነው የሚለው ነው። የአንድ አክሲዮን ዋጋ ትንሽ ሲሆን የባለቤቱ ቁጥር ይቀንሳል። ዋጋው ሲቀንስ ደግሞ የባለአክሲዮኖች ቁጥር ይጨምራል ሲሉ ያስረዳሉ።

የአክሲዮኑ ዋጋው ሲጨምር ደሀው ማኅበረሰብ ላይሳተፍ ይችላል። ከኢትዮ ቴሌኮም ግን ከ10 ሺህ ብር ጀምሮ ሰው ድርሻ ሊገዛ ይችላል። በዚህም በተሳትፎ ደረጃ በርካታ ሰዎችን ያሳትፋሉ። በኢኮኖሚ እይታ ግን ጥቅሙ ዝቅተኛ ነው። ዓላማው በርካታ ሰው ድርሻውን ገዝቶ በባለቤትነት አገልግሎቶቹን እንዲገዛ እና ያለውን ፉክክር ለማዳከም ይመስለኛል ሲሉ ግምታቸውን ያስቀምጣሉ።

ምናልባት በቀጣይ የኩባንያው ትርፉ ሊጨምር ይችላል። ነገር ግን አሁን ባለው ትርፍ አያዋጣም። ሰው አክሲዮኑን ቢገዛ ጥሩ ነው። ነገር ግን በተጋነነ ዋጋ ከሚቀርብ አንድ አክሲዮን በ100 ቢቀርብ ጥሩ ነበር ይላሉ።

የኢኮኖሚ ባለሙያ እና የፖሊሲ አማካሪው ዶክተር ቆስጠንጢኖስ በርኸተስፋ (ዶ/ር) በበኩላቸው እንደሚሉት፤ ኢትዮ ቴሌኮም እያደረገ ያለው አሳታፊነትን ለማሳየት የታሰበ ነው። ምክንያቱም ኢትዮ ቴሌኮም አክሲዮኑን ያቀረበበት መነሻ ዋጋ ትንሽ ነው። እናም አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ሊገዛው የሚችል ነው።

10 በመቶውን ድርሻ በመሸጥ የታሰበው 30 ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ ነው። በዚህም ኩባንያው አሰራሩን ለማዘመን፤ አዳዲስ እቃዎችን ለማስገባት እና አገልግሎቶችን ለማስጀመር በተለይም ከሰው ሰራሽ አስተውሎት ጋራ ሰፋ ያሉ ስራዎች ስለሚጠበቁ ለዛ ሊውል ይችላል። በሌላ በኩል ደግሞ ኢትዮ ቴሌኮም የመንግስት እንደመሆኑ፤ ገንዘቡን ለማሰባሰብ የፈለገበት ምክንያት ሊኖር ይችላል ሲሉ ሀሳባቸውን ያስቀምጣሉ።

ኢትዮ ቴሌኮም አትራፊ ድርጅት ከመሆኑም በተጨማሪ ከፍተኛ ግብር ከፋይ ነው። የሚሉት ባለሙያው፤ የአክሲዮን ዋጋው ዝቅተኛ መሆን አብዛኛው ኢትዮጵያዊ በቁጠባ ሂሳቡ ላይ ያለውን ገንዘብ ሼሩን በመግዛት የተሻለ ውጤት እንዲያገኝ ያስችላል ይላሉ።

ቆስጠንጢኖስ ዶ/ር እንደሚገልጹት፤ ኢትዮ ቴሌኮም ሆነ መንግስት ከአክሲዮን ሽያጭ በሚገኘው ገንዘብ ሌሎች ፕሮጀክቶችን ለማስፋፋት ያስችለዋል። አክሲዮኑን ገዢዎች በሰባት በመቶ ወለድ 300 ብር ባንክ ቢያስቀምጥ የሚያገኘው ገንዘብ እና ኩባንያው በዓመቱ አትራፊ ሆኖ የሚሰጠው ገንዘብ ከዚህ የበለጠ ነው።

ባንኮች በያመቱ ለባለ አክሲዮኖች ከ40 እስከ 60 በመቶ ድረስ የትርፍ ክፍፍል ይሰጣሉ። ስለዚህ አንድ ሰው ብሩን ባንክ አስቀምጦ ሰባት በመቶ ወለድ ከሚያገኝ፤ የባንኮቹን አክሲዮን ቢገዛ የተሻለ ገንዘብ ያገኛል ሲሉ ባለሙያው ያስረዳሉ።

ለምሳሌ አንድ ሰው ብሩን ባንክ ከሚያስቀምጥ የ100 ብር የባንክ አክሲዮን ቢገዛ 60 በመቶ የሚያተርፍ ከሆነ በዓመት 60 ብር ያገኛል። በሁለት ዓመት ገንዘቡ ተመላሽ ይሆናል ወይም ደግሞ አክሲዮኑ እጥፍ ይሆናል። ነገር ግን ይሄ ብር ባንክ ቢቀመጥ 14 ብር ብቻ ነው የሚያገኘው ሲሉ ይገልጻሉ።

ቆስጠንጢኖስ (ዶ/ር) እንደሚገልጹት፤ ኩባንያው እንደ ፋብሪካ እቃ ብቻ የሚያመርት ወይም አገልግሎት ብቻ የሚሰጥ አይደለም። ስልክ የመደወል አገልግሎት፣ የኢንተርኔት አገልግሎት እና ሌሎች የተለያዩ ዘርፎች ላይ ይሰራል። ወደፊት የክሪፕቶ ገንዘቦች ወደ ስራ ከመጡ እነሱን ይጠቀማል። ስለዚህ ድርጅቱ አትራፊ ስለሆነ አክሲዮን ገዢዎች ተጠቃሚ ናቸው።

ለሕዝብ የዞረው ድርሻ 10 በመቶ እንደ መሆኑ ባለአክሲዮኖች በዓመት የሚያገኙት የትርፍ ድርሻ 10 በመቶ ነው። ለአብነትም ኩባንያው 100 ብር ቢያተርፍ 90 ብሩ የኩባኒያው ሲሆን 10 ብሩ ደግሞ የባለአክሲዮኖች ነው ሲሉ ያስረዳሉ።

በመንግስት የተያዙ ድርጅቶች ለግሉ ዘርፍ በማዛወር መንግስት በዋና ስራዉ እንዲያተኩር ነው። ሀገር የመጠበቅ፣ ሕዝብ የማስተዳደር እና ሕዝብ ከድህነት ወለል እንዳይወርድ የማድረግ ስራዎች ለመስራት እና በአክሲዮን ሽያጭ በሚገኘው ገቢ ደግሞ ሌሎች የልማት ስራዎችን ለመስራት ታስቦ ነው ካፒታል ማርኬት የተቋቋመው ይላሉ።

ሌላው ደግሞ ድርጅቶቹ ከመንግስት ቁጥጥር ሲወጡ፤ እነዚህን ድርጅቶች መንግስት በተለያዩ መንገድ ሲያደርግላቸው ከነበረው የድጎማ ጫና ይወርዳል። አብዛኛው ስራ በተቋሙ የሚሰራ እንደመሆኑም የተቋሙን አቅም ለማጠናከር ይረዳል በማለት ይናገራሉ።

ዶክተር ቆስጠንጢኖስ እንደሚገልጹት፤ መንግስት ኢትዮ ቴሌኮምን በከፍተኛ ሁኔታ ሲደጉም ነው የኖረው፤ ሶስት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ዶላር ከቻይና ተበድሮ ነው እስካሁን ድረስ ኩባንያውን በዘመናዊ መልክ ያቋቋመው። ካሁን በኋላ ግን ኩባንያው አክሲዮን እየሸጠ ስራውን እያስፋፋ ይሄዳል። ሁለተኛ ደግሞ ለመንግስት ፈሰስ እያደረገ በማኅበራዊ ልማት ውስጥ ይሳተፋል። በተጨማሪም የግል ዘርፉ በማይገባበት ዘርፍ መንግስት እየገባ ይሰራል በማለት ያስረዳሉ።

ማህበራዊ

# ሴቶች

# ታዳጊዋ የስዕል መምህር

አመስወርቅ ከበደ

ገና ልጅ እያለች ነበር የሕይወት መክሊቷ ሰአሊነት መሆኑን ልትገነዘብ የቻለችው። ልጅ እያለች እርሳስ በማንሳት፤ አሻንጉሊት እና ሌሎች ነገሮች ስዕል መሳል መለማመድ መዝናኛዋ ነበር፤ ምንም እንኳን ቤተሰብ ከትምህርቷ ይልቅ ወደ ስዕል ማዘንበሏን ባይወዱቱም እሷ ግን ሰአሊ የመሆን ፍላጎቱ ስላየለባት ወደ ሰአሊነት ሊወስዳት የሚችለውን መንገድ ከማፈላለግ አልቦዘነችም።

አሁን በታዳጊ ዕድሜዋ የስዕል ትምህርት በተማረችበት ትምህርት ቤት፤ የማስተማር እድል አግኝታ እያስተማረች ሲሆን፤ በተለያዩ ኤግዚቢሽኖች ስዕሎቿን ለእይታ አቅርባለች፤ አንዳንድ ስዕሎችን በ10 ሺዎች በሚያወጣ ገንዘብ ለመሸጥ ችላለች።

ለዛሬ የሴቶች ገጽ ያቀረብናት ባለታሪካችን ሚሊዬን ተክላይ ትባላለች። ትውልድና እድገቷ አዲስ አበባ ከተማ ሲሆን አሁን ላይ 19 ዓመቷ ነው።

ከሚሊዬን ጋር የተገናኘነው በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ14ኛ ግዜ፤ በኢትዮጵያ ደግሞ ለ12ኛ ግዜ ሴቶችና ማኀበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ባዘጋጀው "ታዳጊ ሴቶች ላይ መስራት የነገን የተሻለች ሀገር መገንባት ነው "በሚል መሪ ቃል ዓለም አቀፍ የታዳጊ ሴቶች ቀን ላይ በተዘጋጀው ኤግዚቢሽን ላይ የስዕል ስራዎቿን እያቀረበች ነበር።

በልጅነቷ ለስዕል ያላት ፍላጎት ከፍተኛ ስለነበር ባገኘችው አጋጣሚ ስዕሎችን ትስል ነበር። እያደገች ስትመጣ፤ ወደ ስዕል ትምህርት ቤት ገብታ የስዕል ስልጠና በመውሰድ በቀለም ሸራ ላይ መሳል እንደጀመረች ታስረዳለች።

"እንደ አብዛኛው የኢትዮጵያ ቤተሰብ የኔም ቤተሰቦች ለኪነ ጥበብ ያለኝን ፍቅር አይደግፉም። ቤተሰቦቼ የበለጠ ፍላጎታቸው መደበኛው ትምህርቴ ላይ ትኩረት እንዳደርግ ነው። ነገር ግን ፍላጎት ሲኖር በራስ አቅም ለማስኬድ ጥረት ማድረግ አይቀርም። እኔም ቤተሰቦቼ ስላማይደግፉኝ በራሴ ነው ለመውጣት እየሞከርኩ የነበረው። " ትላለች።

ሚሊዬን አሁን ላይ የተለያዩ ስዕሎች እየሳለች በተለያዩ ኤግዚቢሽኖች ማቅረብ መጀመሯ፤ በስራዋም ውጤት እያስመዘገበች መሆኑ የቤተሰቦቿን ይሁንታ እንድታገኝ እያደረጋት ነው። " አሁን ላይ የቤተሰብ ድጋፍ አለ። ስራዎቼን ሲመለከቱ መደገፍ ጀምረዋል፤ ነገር ግን እስከምወጣ ድረስ በራሴ ነበር ጥረት ሳደርግ የነበረው። " ስትል ትገልጻለች።

መጀመሪያ ላይ ወደ ስዕል ትምህርት ቤት ልትገባ የቻለችው፤ በአንድ ድርጅት ድጋፍ እንደሆነ የምትገልጸው ባለታሪኳ፤ "መጀመሪያ ወደ ስዕል ትምህርት መግባት የቻልኩት በአንድ ድርጅት አማካኝነት ነበር። ወደዛ ሄጄ የስዕል ተስጦ እንዳለኝ ነገርኳቸው እና እንዲያስተምሩኝ አደረኩ። " ስትል ትገልጻለች።

"ለቤተሰቦቼ የትምህርት ክፍያው ከእነሱ እንዳልሆነ እና ያነጋገርኩት ድርጅት እንደሚከፍል ተናግሬ፤ መማር አለብኝ ስላቸው ፈቀዱልኝና ገባሁ። ኮርሱ የሚሰጠው ክረምት ላይ ነው። ቤተሰቦቼ ይችን ክረምት ተምረሽ ወደ መደበኛው ትምህርትሽ መመለስ አለብሽ ይሉኛል። እኔ ግን በአንደበቴ እሺ ብልም ከስዕል መላቀቅ ከባድ ሆኖብኛል። " ስትል ታስረዳለች።

"በልጅነቴ የስዕል ስልጠናውን ስከታተል የነበረው አቢሲኒያ ትምህርት ቤት ነበር፤ ከፍ እያልኩ ስመጣ ደግሞ አሁን ወደ ማስተምርበት የስዕል ትምህርት ቤት ገብቼ የሸራ ስዕሎችን፣ የስዕል ነድፎች እና ቀለም መቀባት በደንብ ተምሬ ስዕል መስራት ጀምርኩ" ትላለች።

"የመጀመሪያውን አቢሲኒያ የወሰድኩትን ስልጠና እንድከታተል የከፈለልኝ አንድ ድርጅት ነው። ሁለተኛውን የገባሁት 10ኛ ክፍል እየተማርኩ ነበር፤ የሁለተኛውን ክፍያ ታላቅ እህቴን አናግሬ እሷ ናት የከፈለችልኝ። ስልጠናውን ስወስድ የነበረው ክረምት ላይ ነው። መጀበኛው ትምህርት ሲጀምር የስዕል ስልጠናውን ቅዳሜና እሁድ አደረግኩት። ስለዚህ ቅዳሜና እሁድ ነው የተማርኩት ስትል። " ታስረዳለች።



ሚሊዬን ተክላይ

"የሁለተኛውን ስልጠናዬን ከመጀመሬ በፊት በእርሳስ ብቻ ነበር የምስለው። ሁለተኛውን ስልጠናዬን ከጀመርኩ በኋላ በብዙ ነገር ለመሻሻል ቻልኩ። ስዕል መስራት፣ በኤግዚቢሽኖች ማሳየት እና መሸጥ ጀመርኩኝ ስትል ትናገራለች።

ሚሊዬን አሁን ላይ የስዕል ስራዎቿ በተለያዩ ውድድሮች ቀርበው አሸናፊ ሆነዋል። የተወሰኑ ስዕሎችንም በኤግዚቢሽኖች ላይ መሸጧን በመግለፅ፤ "እስካሁን ድረስ የተሸጡትን ሳይጨምር 10 ስዕሎችን ሰርቻለሁ። ሁለት ስዕሎችን ደግሞ የሸጥኩ ሲሆን፤ አንዳንድ ግዜ ውድድሮች ላይ ስዕሎቹ ሲያሸንፉ ዋጋቸውም በዚያው ልክ ይጨምራል። ውድድሩን በማሸነፌ የሚሰጠኝ ሽልማት እንዳለ ሆኖ ማለት ነው። "ትላለች።

እስካሁን ድረስ ሁለት ውድድሮች ማሸነፍ እንደቻለች በመግለጽ፤ ባለፈው ዓመት በክፍለ ከተማ ደረጃ ከኪነ ጥበብ ጋር ተያይዞ በተዘጋጀ ዝግጅት ላይ ተወዳድራ አሸናፊ መሆን ችላለች። ከዛ በፊት ደግሞ በትምህርት ቤት ደረጃ በተደረገ ውድድር አሸንፌአለሁ ስትል ታስረዳለች።

"እካሁን "አብስትራክት" የሆኑ ስዕሎች ወደ መሳል አልገባሁም። አሁን ላይ እየሳልኩ ያለውት በግልፅ መረዳት የምንችላቸው የስዕል አይነቶችን ነው የምሰራው። "በማለት ትገልጻለች።

ሚሊዬን ኤግዚቢሽኖች ላይ ስዕሎችን ማቅረብ ያስደስታታል። በአንድ ወቅትም ሴት ልጅ አትችልም የሚለውን አመለካከት ለመስበር የታሰበ እና የታዳጊ ሴቶች ቀንን አስመልክቶ በሕዝብ ተቀባይነትን ያገኘ ኤግዚቢሽን አቅርባለች። እኛ ይህንን ጽሁፍ ለማዘጋጀት በተገኘንበት ወቅትም ልዩ ልዩ ስዕሎችን አቅርባ ተመልክተናል። ስለስዕሎቹም ሚሊዬን እንደምትናገረው "ዛሬ ያቀረብኩት ስዕል ስለ ጥበበኛ ሴት ወይም የተለያየ የጥበብ ስራዎችን ስለምትሰራ ሴት ነው። ሴቶች በርካታ የእጅ ሙያ ጥበብ አላቸውና ይህን ለመግለጽ ነው። " ስትል ታስረዳለች።

"ሚሊዬን አሁን በተማረችበት ትምህርት ቤት የስዕል ትምህርት ታስተምራለች። የማስተምረው ከእኔ እድሜ የሚያንሱትን እና እኩዮቼን ነው። እኔ እስከምችለው ድረስ ሳስተምር ትንሽ ጠንከር የሚለውን የትምህርት ክፍል የሚያስተምረው ደግሞ ዋናው መምህር ነው። " ትላለች።

"ከእድሜ አንጻር ተማሪዎቼ የማስተማር አቅሜ ላይ ጥርጣሬ የላቸውም። ምክንያቱም እኔ እንደ ጓደኛ ስለምቀርባቸው፤ ስንተኛ ክፍል እንደሆንኩ እና የት የት እንደተማረኩ ስለሚያውቁ በምሰጣቸው ትምህርት ላይ ነው ትኩረታቸውን የሚያደርጉት እንጂ ከእኛ ትንሽናት ወይም እኩያችን ናት ብለው የሚያሳዩት

**አሁን ላይ የስዕል ስራ ለሚሊዬን የውስጧ ፍላጎት በመሆኑ ለማሳካት የምትጥረው ጉዳይ ብቻ ሳይሆን፤ ገቢ የምታገኝበት ስራዋ፣ ውሎዋ፣ አድናቆት የምታገኝበት እና አዲስ ምዕራፍ የሚያሳያት መንገድ የሆነ ይመስላል**

የተለየ ነገር የለም። " ስትል ትናገራለች።

አሁን ላይ የስዕል ስራ ለሚሊዬን የውስጧ ፍላጎት በመሆኑ ለማሳካት የምትጥረው ጉዳይ ብቻ ሳይሆን፤ ገቢ የምታገኝበት ስራዋ፣ ውሎዋ፣ አድናቆት የምታገኝበት እና አዲስ ምዕራፍ የሚያሳያት መንገድ የሆነ ይመስላል። ሚሊዬን በምታስተምርበት ትምህርት ቤት በሰራችው ልክ ክፍያ ይሰጣታል።

"እኔ የተቀጠርኩት አስተማሪዬ ለፕሮጀክት ስራ በሚወጣበት ወቅት ነው። ስለዚ ዋናው አስተማሪ ከሰራሁ ፕሮጀክት ከሚያገኘው ገቢ፤ ባገኘው ገንዘብ መሰረት ለእኔም በሰራሁት ልክ ይታሰብልኛል። " ትላለች።

ከዚህ በተጨማሪ በተለያዩ ኤግዚቢሽኖች የስዕል ስራዎቿን አቅርባ ኤግዚቢሽኑን ሊመለከቱ የመጡ ሰዎች የወደዷቸውን ስዕሎች ገዝተው ይሄዳሉ። በዚህም አንድ ስዕል እስከ 25 ሺህ ብር ድረስ እንደምትሸጥ ትገልጻለች።

የስዕል ትምህርቱን የምታስተምረው፤ ትምህርት ሲዘጋ ክረምት ላይ ሲሆን ክረምት ከተጀመረ በኋላ ቅዳሜና እሁድ የማስተማር ስራው ይቀጥላል። "ክረምት ላይ የስዕል ኮርስ እንሰጣለን፤ ሐምሌ፣ ነሐሴ እና መስከረም ላይ ትምህርት እስከሚጀምር ድረስ እናስተምራለን። ከዛ በኋላ ቅዳሜ እና እሁድ ነው የምናስተምረው። እኔ በሁሉም ወቅት እሰራለው ስትል። " ትናገራለች።

"በስዕል ትምህርት ላይ የበለጠ ማተኮሬ ከመደበኛው ትምህርቴ ጋር ተጋጭቶብኛል የምትለው ሚሊዬን፤ የመደበኛው ትምህርቷን ግዜና ፍላጎት እንደተሻማባት ታስረዳለች። በዚሁ የተነሳ ባለፈው ዓመት የ12ኛ ክፍል ማትሪክ ተፈትና ውጤት አላምጣችም። ወደ ፊት ትምህርቷን የማሻሻል ፍላጎት ቢኖራትም በስዕሉ እየገፋች ስለሆነ በውጤቱ ብዙም እንዳልተከፋች ታስረዳለች።

ቤተሰቦቿ አሁን ላይ ለስዕል ያላትን ጥልቅ ፍቅር ስለተገነዘቡ ጫና ማሳደሩን መተዋቸውን ስትገልጽ፤ እንዲህ ትላለች፤ "ቤተሰቦቼ ተስማምተውበት ሳይሆን የውስጤ ፍላጎት አርት መሆኑን ስለተገነዘቡ እና ስራዎቼን ሲመለከቱ፤ የምትፈልገውን ታደርግ በሚለው ስለተውኝ አሁን የቤተሰብ ተጽኖ የለብኝም። " ትላለች።

"በስዕል ውድድር ላይ ቀርበው የተሸለሙት ስዕሎቿ ሁለቱም ሀገራዊ ሀሳብ የያዙ ናቸው። አንደኛው በክፍለ ከተማ ደረጃ የተወዳደረው ስለ ኢትዮጵያ ሰለም የሚተርክ ሲሆን፤ ሁለተኛው በትምህርት ቤት ደረጃ የቀረበው ስእሷ በሕብረ ብሔር ያሸበረቀች ኢትዮጵያ የሚል ነው። ይህንንም ስዕል የሰራችው ሀገር በሴት ስለምትመሰል ሀገርን በአንዲት ሴት ወክላ ነው። " ስትል ታስረዳለች።

ስራዋን በምትሰራበት ወቅት ብዙ የሚፈትኗት እና ተግዳሮት የሚሆኑባት ነገሮችም አልጠፉም። በስዕል ስራዋ ላይ ያጋጠማት ተግዳሮት፤ የመጀመሪያው የቤተሰብ ተጽዕኖ ነው። ሌላኛው ደግሞ ስዕል ከመደበኛ ትምህርቷ ጋር ማስኬድ ነው፡ ለስዕል የሚያስፈልጉ ግብዓቶች ዋጋ ውድ መሆንም ሌላው ችግር ነው።

አንዴ ወጥታ ስራዎቿ መታየት እስኪጀምሩ ያሉ ነገሮች ከባድ መሆናቸውን በመግለጽ፤ ዋናው ነገር ግን ወደ ሚፈለገው ቦታ ለመድረስ መጣር እና መቼም ቢሆን ተስፋ አለመቁረጥ ጠቃሚ ነገሮች መሆናቸውን እንደምክር ታስቀምጣለች።

"የስዕል ስራዬን የምሰራው ማታ ነው። አስፈላጊ ከሆነ እየሰራው ላነጋም እችላለው። " ትላለች። የምስላቸው ስዕሎችም ከውስጥ ስሜቷ የመነጩ ወይም ደግሞ በትዛዝም ሊሆን ይችላል። ዋጋቸው እንደ መጠናቸው ይለያያል። ብዙዎቹ ግን እስከ 20 እና 25 ሺህ ብር ድረስ የሚሸጡ ናቸው። የምታገኘውን ገንዘብ ግን መልሳ የምታውለው ለስዕል ስራ ነው።

ቀጣይ ሕልሟ ተጨማሪ የስዕል ትምህርት ተምራ የግሏን ስራ መጀመር እንደሆነ ትናገራለች። « ቀጣይ ሕልሜ ተጨማሪ የኪነጥበብ ትምህርት ተምሬ በመጨረስ፤ የራሴ የሆነ ትልቅ የስዕል መማሪያ መክፈት ነው። »ስል ሃሳቧን ቋጭታለች።

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

### ግርማ መንግሥቴ

አዲስ ዘመንን ይዞ ምን ጎድሎ እንዲሉ ነውና የዛሬው "አዲስ ዘመን ድሮ" የተለያዩ፤ ምናልባትም የሚያዝናኑ ርእስ ጉዳዮችን ጭምር ይዞ ቀርቧል። በተለይ የአዳኞች "የማእረግ ስም" እና "ሹመት"፣ ማህበራዊ ስፍራቸው፤ የኢራኑ ንጉሥ፣ የጫጉላ ሽርሽራቸውና የጦርነቱ ድግስ በትውስታ ፈገግ ያደርጋሉና እንደሚከተለው ቀርበዋል።

### ጆሞ ኬንያታ

በዚህ ወር ውስጥ ስለ ኬንያ ሕገ መንግሥት ጉዳይ በለንደን በሚደረገው ስብሰባ ላይ የቀድሞው የማኡ ማኡ መሪ ጆሞ ኬንያታ ተካፋይ እንዲሆን መንግሥቱ ባይፈቅድም ቅሉ ከኬንያታ አንድ ማስታወሻ በአፍሪካ ምክር ቤት አባሎች በኩል ወደ ለንደን ይላካል ሲሉ የኪኪዩ መሪ ዶክተር ጊኮንም አስታውቀዋል።

የሰባቱ አውራጃ የፖለቲካ ማህበር መሪዎች ባደረጉት ስብሰባ ላይ ለንደን ላይ በሚደረገው ስብሰባ ተካፋዮች ለሚሆኑት ለአፍሪካ መልእክተኞች መሪ ጆሞ ኬንያታ መሆን አለበት ያለ በለዚያ ግን ምንም አይነት ስብሰባ አይደረግም ሲሉ ንግግራቸውን ደምድመዋል።

በዚህም ምክንያት ለአፍሪካ መልእክተኞች መሪ እንድትሆን ተመርጠሃል የሚል ቴሌግራም ለጆሞ ኬንያታ የተላከ መሆኑ ታውቋል።

(ጋዜጣው በዚሁ ዐቢይ ርእስ ስር የሚከተለውን ንኡስ ርእስ አያይዞ አቅርቧል።)

### አፍሪካ ከአሥር ዓመት በኋላ

የታንጋኒካ ናሲዮናሊስት መሪ በቢቢሲ ሲናገሩ በሚቀጥሉት አስር ዓመታት ውስጥ አፍሪካ በሙሉ ነፃ ትወጣለች ካሉ በኋላ አፍሪካ በሙሉ ነፃ ከሆነች በኋላ የውጭ ሀገር ተወላጆች (ነጮች) በአፍሪካ እንዲቀመጡ ትፈቅዳላችሁን? በማለት ለተጠየቁት ጥያቄ ሲመልሱ በእርግጥ ይፈቀድላቸዋል፤ ብለዋል።

(አዲስ ዘመን፣ ታህስ 30 ቀን 1952 ዓ/ም)

### አደንና አዳኝ

ምንም እንኳን በሀገራችን በአሁኑ ጊዜም ቢሆን በሌላው ዓለም ውስጥ የሌሉ በጣም ብርቅዬ የሆኑ የዱር እንስሳት ቢገኙም፤ ከጥንቱ ጋር ሲወዳደር ግን በቁጥርም ሆነ በአይነት በጣም አናሳ መሆናቸው በተለያዩ ጊዜያት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ክፍሎች ተገልጿል። ለዚህም የዱር እንስሳት ቁጥር እያቆለቆለ መሄድ ዋነኛው ምክንያት ኋላ ቀር የነበረው ሥርዓት የወለደው ልማድና ወግ መሆኑ አጠያያቂ አይደለም። ባለፉት መቶ ዓመታትና ከዚያም በፊት ባህሉ በፈጠረው መሠረት በህብረተሰቡ ውስጥ ሙያቸውን አደን ያደረጉ ሰዎች እንደ አደኑት እንስሳ አይነትና መጠን ከህብረተሰቡ ልዩ ክብርና ሙገሳ ስለሚሰጣቸው ነው። ለአብነትም ያህል የሚከተለውን እንመልከት።

**ሀ• ዝሆን ገዳይ** - አዳኙ 40 ሰው እንደ ገደለ ይቆጠርለታል።

**ለ• አውራሪስ ገዳይ** - አዳኙ 15 ሰው እንደ ገደለ ይቆጠርለታል።

**ሐ• አንበሳ ገዳይ** - አዳኙ 5 ሰው እንደ ገደለ ይቆጠርለታል።

**መ• ቀጭኔ ገዳይ** - የቀጭኔ ገዳይ ሚስት በውሃ መቅዳት ላይ ቅድሚያ ይሰጣታል።

**ሠ• ግሥሳ ገዳይ** - ግስላ ገዳይ ሳይፎክር ቀድሞ የሚነሳ የለም።

**ረ• ተኩሳ ገዳይ** - ሌሎች ገዳዮች እየፎከሩ ሳሉ ተኩሳ ገዳይ ቢነሳ ሁሉም ዝም ይላል።

**ሰ• ነብር ገዳይ** - ነብር እሰው አጥር ጊቢ ገብቶ ሴት ገደለችው የሚል ንግርት ስላለ ገዳዩ ለ15 ቀን ብቻ ቅቤ ይቀባል።

(አዲስ ዘመን፣ መስከረም 9 ቀን 1980 ዓ/ም)

### ኢራክና ኢራን

ኢራክና ኢራን "ሻቴል ዓረብ" በተባለው የባህር ዳርቻ ምድር የተነሳ የወሰን ግጭት አንስተዋል፤ "ሻቴል ዓረብ" የጤግሮስና የኤፍራጥስ ወንዞች" "ፐርሺያን ጋልፍ" ከተባለው የባህር ሰላጤ ጋር በሚገናኙበት ቦታ ላይ የሚገኘው ክፍለ ሀገር ነው። በዚህ ስፍራ አቅራቢያ የኢራን ዋና የዘይት ማውጫ ማእድን ይገኝበታል፤ ነገር ግን የኢራክ መንግሥት በዚህ ስፍራ ውስጥ 3 ማይል ያህል ስፋት ያለው መሬት የኔ ነው ስትል ሃሳቧን ገልጣለች፤ በዚህ ምክንያት በዚህ ወሰን አጠገብ የኢራን መንግሥት የመከላከያ ኃይሏን ማከማቸት ይዛለች።

ኮራማሻይር በተባለ ታላቅ የንግድ ወደብ ዙሪያ ብዙ የጦር ኃይል በዚህ ከተማና በኤባዳን ከተማ ዙሪያ ተጠራቅሟል። የባህሩን ሰላጤ እያለፉ ወደ ጤግሮስና ወደ ኤፍራጥስ ወንዝ የሚሄዱት የንግድም ሆኑ የመንገደኛ መርከቦች በኢራን ጠረፍ ሲደርሱ እየተፈተሹ ነው እንጂ እንዲያው መተላለፍ አይቻልም፤ መከላከያው ኃይል በተከማቸበት ስፍራ ወታደሮች እንጂ ሲቪል ሊተላለፍ አይችልም፤ ፈቃድ የተሰጣቸው ወታደሮች ሁሉ በንቃት ታጥቀው እንዲጠባበቁ ተደርጓል።

ኢራክም በበኩሏ ይህንን ነገር ተመልክታዋለች፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሜጀር ጀነራል ቃሲም "ኢራን ፀብ በማንሳት ሠላምን ለማጥፋት ተነሥታለች፤ ለሚመጣው ሁሉ ሃላፊነቱ የኢራን ነው። እስካሁን ድረስ ወደ ወሰኑ የጦር ኃይል (አላክንም)፤ ወረራ ከመጣብን ግን ወራሪ ጠላታችንን ለማጥፋት ደቂቃ እንኳን አይወስድብንም፤ በወሰናችን ላይ የጦር ኃይል አለማከማቻታችንን መላው ዓለም ይመሰክርልናል" ሲሉ ተናግረዋል።

የኢራን ንጉሥ ግን 3ኛ ሚስታቸውን ካገቡ ገና ስምንት ቀን ሆናቸው፤ ንግሥቲቱን ይዘው የጫጉላ ጊዜአቸውን ለማሳለፍ ወደ ካስፒአን ባህር ጠረፍ ሄደዋል፤ ንጉሡ ለ10 ቀን ያህል ከሙሽራዪቱ ጋር ሲያድኑ፣ ፈረስ ሲጋልቡና በጀልባ ሲንሸራሸሩ እንደሚቆዩ ተነገረ። ንጉሡና ሙሽራዪቱ ወደ ካስፒአን ባህር መሄዳቸው በኢራንና በኢራክ መካከል ያለው ግጭት የማያሰጋ መሆኑን ያመለክታል።

(አዲስ ዘመን፣ ታህሳስ 21 ቀን 1952 ዓ/ም)

# ዓለም አቀፍ

## እስራኤል በኢራን ላይ ያቀደችውን ጥቃት አሜሪካ የገመገመችበት ሰነዶች ሾልከው ወጡ

እስራኤል በኢራን ላይ ጥቃት ለመፈጸም ማቀዷን አሜሪካ የገመገመችበት ምሥጢራዊ ሰነዶች እንዴት ሾልከው እንደወጡ ምርመራ መከፈቱን የሀገሪቱ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈጉባኤ ማይክ ጆንሰን ገለጹ። ኢራን መስከረም 21 ቀን 2017 ዓ.ም ለፈጸመችው የሚሳዔል ጥቃት ምላሽ ለመስጠት እስራኤል ወታደራዊ ንብረቶችን ማንቀሳቀሷን የሚያሳዩ የሳተላይት ምሥሎችን የያዙ ሰነዶች ባለፈው ሳምንት ከኢራን ጋር ግንኙነት ባለው ቴሌግራም ገጽ ላይ ለህትመት በቅተዋል።

በከፍተኛ ምሥጢር እንደተያዙ የሚያመለክቱት እነዚህ ሰነዶች በአሜሪካ፣ በዩናይትድ ኪንግደም፣ በካናዳ፣ በኒውዚላንድ እና በአውስትራሊያ የደህንነት እና የስለላ ጥምረት ብቻ እንዲታዩ የሚገልጽ መሆኑን ተዘግቧል። ኢራን በመቶዎች የሚቆጠሩ ሚሳዔሎችን ወደ እስራኤል አስወንጭፋ ጥቂቶቹ የእስራኤልን ግዛት እንደመቱ ይታወሳል።

ለሳምንታት እስራኤል ኢራን ለፈጸመችባት ጥቃት እንዴት እና መቼ ምላሽ እንደምትሰጥ ስታሰላስል መቆየቷ ተዘግቧል። የእስራኤል የመከላከያ ሚኒስቴር ምላሹ “የከፋ እና ድንገተኛ እንደሚሆን” ሲያስጠነቅቅ ነበር። ሁለቱ ሾልከው የወጡ ምሥጢራዊ ሰነዶች የአሜሪካ ብሔራዊ ደህንነት ኤጀንሲ (ኤንኤስኤ) እና ብሔራዊ ጂኦስፓሺያል ኢንተለጀንስ ኤጀንሲ ግምገማ ያደረጉባቸው እንደሆነ ሪፖርት ተደርጓል።

ሰነዶቹ “ሾልከው መውጣታቸው አሳሳቢ ነው” ሲሉ የተናገሩት አፈ ጉባኤው ጆንሰን ሀገራቸው በዚህ ጉዳይ ላይ ምርመራ እያካሄደች መሆኗን መናገራቸው ተዘግቧል። ፔንታጎን ሰለ ሰነዶቹ የወጣውን ሪፖርት እንደሚያውቅ ቢያረጋግጥም ተጨማሪ አስተያየት ከመስጠት ተቆጥቧል።

በግምገማው ላይ ተሳትፈዋል የተባሉት የአሜሪካ ተቋማት እንዲሁም የእስራኤል መንግሥት ሾልከው ስለወጡት ሰነዶች በይፋ የሰጡት አስተያየት የለም። ሰነዶቹ ሾልከው መውጣታቸውን መጀመሪያ የዘገቡት



ሲኤንኤን እና አክሲዮስ ሚዲያዎች ሲሆኑ፣ በዚህም አሜሪካ የቅርብ አጋሯን እስራኤልን እንደምትሰልል በድጋሚ የሚያረጋግጥ ነው ተብሏል።

አንደኛው ሰነድ አሜሪካም ሆነ እስራኤል በይፋ የማያምኑት የእስራኤልን የኑክሌር አቅምን የሚያመለክት ሲሆን፣ በየትኛውም ጥቃት የኑክሌር መሣሪያን መጠቀምን አማራጭ ይከለክላል። እነዚህ ሰነዶች አሾልኮ የወጣበት መንገድ በኢራን ላይ የታቀደውን የበቀል ጥቃት መጠን ለማጋለጥ ወይም ምናልባት ለማደናቀፍ የተደረገ ሙከራ እንደሆነ አንድ የቀድሞ የአሜሪካ የስለላ ባለሥልጣን ለቢቢሲ ገልጸዋል።

አሜሪካ መረጃው ሆን ተብሎ በአሜሪካ የደህንነት ሠራተኛ ይፋ የተደረገ ወይም የተሰረቀ ስለመሆኑ እየመረመች እንደሆነና ምናልባትም በምዝበራ ተገኝቶ ሊሆን እንደሚችል ባለሥልጣናቷ ለአሶሼትድ ፕሬስ ተናግረዋል። ሁለቱ ሰነዶች ጥቅምት 5 እና 6 ቀናት 2017 ዓ.ም. በተገኙ የሳተላይት መረጃ ላይ መሠረት ያደረጉ ናቸው።

በሰነዱ ላይ አንደኛው ርዕስ የእስራኤል አየር ኃይል በኢራን ላይ ጥቃት ለመሰንዘር ዝግጅቱን አጠናክሮ መቀጠሉ እና ለሁለተኛ ጊዜ እያደረገ ያለውን ከፍተኛ የኃይል ስምሪት እንደሚያትት የሮይተርስ የዜና ወኪል ዘግቧል።

በዚህም የባለስቲክ እና ከአየር ወደ መሬት የሚወነጨፉ የሚሳኤል ጥቃቶችን ቅንጅትን ሲያብራራ፣ ሁለተኛው ርዕስ የእስራኤል የሰው አልባ አውሮፕላኖች (ድሮኖች) እንቅስቃሴ የሚመለከት መረጃ ይዟል። አርብ ዕለት የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን እስራኤል በኢራን ላይ ልትፈጽመው ስላቀደችው ጥቃት በአንድ ጋዜጠኛ በተጠየቁበት ወቅት “ጥሩ ግንዛቤ” እንዳላቸው ቢናገሩም ዝርዝሩን ከመናገር ተቆጥበዋል።

እስራኤል በኢራን ላይ የበቀል ጥቃት የምትፈጽም ከሆነ በመካከለኛው ምሥራቅ ያለው ቀውስ ይባባሳል የሚል ስጋት ያላት አሜሪካ የእስራኤልን ዝግጅት በቅርበት እየተከታተለች ነው።'ሚድል ኢስት ስፔክቴተር' በተባለው የቴሌግራም ቻናል ላይ ይፋ የሆነው የአሜሪካ የስለላ መረጃ፣ ከወዳጇ እስራኤል ጋር መቃቃርን ሊፈጥር ይችላል የሚል ስጋትን ፈጥሯል።

ምክንያቱም ሾልከው ወጡት ሰነዶች አሜሪካ በተለያዩ መንገዶች ያሰባሰበቻቸው ወታደራዊ የስለላ መረጃዎች በመሆናቸው እስራኤል ስለላ እየተካሄደባት መሆኑን በመግለጽ ተቃውሞ ልታሰማ ትችላለች በሚል ነው። ከአንድ ዓመት በፊት በሀገራት ላይ የተካሄደ የወታደራዊ ስለላ መረጃ በአንድ የአሜሪካ ሠራዊት የደህንነት አባል ሾልኮ ወጥቶ በማኅበራዊ ሚዲያ ላይ ይፋ በተደረገበት ጊዜ ደቡብ ኮሪያ እና ዩክሬንን ጨምሮ የአሜሪካ አጋሮች ቁጣቸውን ገልጸው ነበር።

አሁንም የእስራኤል ወታደራዊ ዝግጅትን በተመለከተ አሜሪካ ያሰባሰበችው መረጃ ለኢራን ቅርብ ነው በተባለ የቴሌግራም ቻናል በኩል ይፋ መሆኑ በእስራኤል ባለሥልጣናት በቀላሉ የሚታይ አይሆንም። እንዲሁም ይህ ክስተት በአሜሪካ በኩል የመረጃ አጠባበቅ ደህንነት ጥያቄን ያስነሳ ሲሆን፣ ይፋ የሆነው ሰነድ ለኢራን ቅርብ በሆነው የማኅበራዊ ትስስር ገጽ ይፋ የሆነው ተሰርቆ ከሆነ አሜሪካ ከኢራን ጋር ወደ ተጨማሪ ውዝግብ እንድትገባ ያደርጋታል ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።

Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ethiopian Press Agency

አዲስ ዘመን
ማክሰኞ
ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# ኢትዮጵያ በታዳጊዎች የሜዳ ቴኒስ ውድድር የወርቅ ሜዳሊያን አስመዘገበች

**ዓስማየሁ ግዛው**

ዓለም አቀፍ የታዳጊዎች ሜዳ ቴኒስ ውድድር በኢትዮጵያ አስተናጋጅነት ለአንድ ሳምንታት ተካሄዶ ተጠናቋል። ኢትዮጵያ በውድድሩ ለመጀመሪያ ጊዜ በወንዶች ጥንድ ፉክክር የወርቅ ሜዳሊያ አስመዝግባለች።

ከሃያ በላይ የዓለም ሀገራት የተሳተፉበት ይህ ውድድር በኢትዮጵያ ቴኒስ ፌዴሬሽንና በዓለም አቀፉ የቴኒስ ፌዴሬሽን ትብብር ከጥቅምት 4 ጀምሮ በአዲስ አበባ ቴኒስ ክለብ ሲካሄድ ቆይቶ ከትናንት በስቲያ ሲጠናቀቅ፣ ሰባት ቀናትን በፈጀው ፉክክር ኢትዮጵያ በአስራ ሦስት ወንድና ስድስት ሴት በድምሩ በ19 ስፖርተኞች ተሳትፋለች።

በሁለቱም ጾታዎች በጥንድና ነጠላ ውድድሮች የሚደረጉ ፉክክሮች ፍፃሜ ሲያገኙ ኢትዮጵያ በወንዶች ጥንድ የወርቅ ሜዳሊያ በማሳካት በስፖርቱ ታሪክ አዲስ ነገር አሳክታለች። ይህን ሜዳሊያ ማስመዝገብ የቻሉትም ዳዊት ሸለመና ዳዊት ፍሰሃ ጥንድ ሆነው ባደረጉት ፉክክር ነው። ሁለቱ ታዳጊ ሞክሼዎች ከጃፓን እና ሕንድ ተወዳዳሪዎች ጋር እልህ አስጨራሽ ፉክክር በማድረግ 64 ለ 25 እና 10 ለ 5 በሆነ ውጤት በማሸነፍ ድል ማድረግ ችለዋል። በዚህም መሰረት በወንዶች ጥንድ ኢትዮጵያ የወርቅ ሜዳሊያውን ለመጀመሪያ ጊዜ ስታሳካ፣ ጃፓንና ሕንድ የብር፣ ግሪክ፣ ፖላንድና ደቡብ ኮርያ የነሐስ ሜዳሊያን አስመዝግበዋል። በሴቶች ጥንድ ውድድር ደግሞ አሜሪካና ሕንድ የወርቅ፣ ብራዚል የብር፣ ኬንያና ሕንድ የነሐስ አሸናፊ መሆን ችለዋል፡፡

በወንዶች ነጠላ ውድድር ጃፓን የወርቅ፣ ሕንድ የብርና ግሪክ የነሐስ ሜዳሊያ በመውሰድ አጠናቀዋል። በሴቶች ነጠላ



**በዓለም አቀፍ የሜዳ ቴኒስ የታዳጊዎች ጥንድ ውድድር ኢትዮጵያውያኑ ዳዊት ሸለመና ዳዊት ፍሰሃ የወርቅ ሜዳሊያን አስመዝግበዋል፣**

እንዲሁ ሕንድና ብራዚል የወርቅና የብር፣ ሕንድና አሜሪካ የነሐስ ሜዳሊያ ወስደዋል፡፡

ከሃያ በላይ ሀገራት ተወጣጡ 19 ሴትና 32 ወንድ በድምሩ 51 ስፖርተኞች ጠንካራ ፉክክርን ባደረጉበት መድረክ በአዋቂዎች መካከል የሚደረገው ውድድር እስከ ጥቅምት 17 የሚቀጥል ይሆናል፡፡

ኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ የቴኒስ ውድድሮችን ስታዘጋጅ የመጀመሪያዋ አይደለም። በታዳጊዎች ለአራተኛ ጊዜ እንዲሁም በአዋቂዎች ለሁለተኛ ጊዜ በጥቅሉ ለስድስት ጊዜያት ዓለም አቀፍ ውድድሮችን ማስተናገዳ ይታወቃል፡፡

የኢትዮጵያ ሜዳ ቴኒስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት አቶ ታምራት በቀለ፣ በመጀመሪያው ዙር የታዳጊዎች ውድድር ማጠናቀቂያና ሁለተኛ ዙር የወጣች ውድድር ማስጀመሪያ መርሃግብር ስነስርዓት ላይ እንደተናገሩት፣ ኢትዮጵያ ውድድሩን በማዘጋጀቷ በርካታ ስፖርተኞችን የማሳተፍ እድል ፈጥሮላታል። ይህም ከሀገር ውጪ የሚደረጉ ውድድሮች ላይ በበጀትና ሌሎች ችግሮች ምክንያት ከሁለት ተወዳዳሪ በላይ ለመላክ እንቅፋት የነበሩ ችግሮችን እንደቀረፈ አክለዋል። በተጨማሪም ኢትዮጵያ በውድድሩ ልምድ ከመቅሰም በላይ ተፎካካሪ ሆና ሜዳሊያ ማስመዝገቧ ስኬት መሆኑን አንስተዋል።

ኢትዮጵያ ውድድሩን ማዘጋጀቷ ከስፖርታዊ ጥቅምም ባለፈ ከተለያዩ ሀገራት በሚመጡ የስፖርት ቤተሰቦች ገጽታዋን ለመገንባትና ስፖርት ቱሪዝምን ለማስፋፋት ትልቅ ሚና እንዳለው አቶ ታምራት ተናግረዋል። በዚህም መሰረት ከዚህ በፊት ከተካሄዱት ውድድሮች አንጻር የማስተናገድ አቅም፣ የመወዳደሪያ ስፍራዎች መሻሻል፣ የተሳታፊ ስፖርተኞች ቁጥር መጨመርና ውድድሩን የማሸነፍ አቅም ከፍ ማለቱን አስረድተዋል፡፡

ኢትዮጵያ ያስተናገደችው ሌላው የ2024 የአፍሪካ ጠረጴዛ ቴኒስ ቻምፒዮናም ከጥቅምት 2 እስከ 9/2017 ዓ.ም በኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ ሲካሄድ ቆይቶ ከትናንት በስቲያ ፍፃሜ ሲያገኝ ኢትዮጵያ ሁለት ሜዳሊያዎችን አስመዝግባለች። በቡድን፣ በድብልቅ ፆታ፣ በጥንድና በነጠላ በአጠቃላይ በሰባት የውድድር ዓይነቶች ሀገራት ተፎካካሪ በሆኑበት በዚህ ቻምፒዮና ኢትዮጵያ ቡድንና በነጠላ ውድድር ጥሩ ተፎካካሪ ሆና ሶስተኛ ደረጃን ይዛ በማጠናቀቅ ሁለት የነሐስ ሜዳሊያዎችን አስመዝግባለች።

ለ27ኛ ጊዜ በተካሄደው የአፍሪካ ጠረጴዛ ቴኒስ ቻምፒዮና ግብፅና ናይጄሪያ የበላይ ሆነው ሲያጠናቅቁ፣ ኢትዮጵያ ካስመዘገበችው የነሐስ ሜዳሊያ በተጨማሪ በነጠላ ውድድር ዱፌራ መኮንን የነሐስ ሜዳሊያ አስመዝግቧል። ተጫዋቹ ከማጣሪያው ጀምሮ ጠንካራ ተፎካካሪ በመሆን ብቃቱን ያሳየ ሲሆን በታሪክ ግማሽ ፍጻሜ በመግባት የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ መሆን ችሏል። በማጣሪያው ፉክክር ተጋጣሚው 4 ለ 1 በሆነ ውጤት በመርታት ወደ ሩብ ፍጻሜ ያለፈው ዱፌራ፣ በሩብ ፍጻሜ ጨዋታ ግብጻዊውን ኤል-ቤኢአሊ መሀመድን 4 ለ 2 በመርታት የግማሽ ፍጻሜ ተፋላሚ ሆኗል። ኢትዮጵያ በውድድሩ በአጠቃላይ ከግብጽ፣ ናይጄሪያና አልጄሪያ በመቀጠል በሁለት ሜዳሊያዎች አራተኛ ደረጃን በመያዝ ውድድሯን አጠናቃለች፡፡

ኢትዮጵያን ይህን ውድድር በማስተናገዷ የማወዳደሪያ ቁሳቁሶች፣ የባለሙያዎች ስልጠና እና ከረጅም ዓመት በኋላ የተመዘገበው አበረታች ውጤት ማግኘት ችላለች። ከውድድሩ ጎን ለጎንም የአፍሪካ ጠረጴዛ ቴኒስ ፌዴሬሽን ጠቅላላ ጉባኤን አስተናግዳ በስኬት ከማጠናቀቋም በተጨማሪ፣ በአህጉር አቀፉ ኮንፌዴሬሽን በምክትል ፕሬዚዳንት ማዕረግ የሚዲያና ሕዝብ ግንኙነት ኃላፊነት ቦታን መያዝ ችላለች፡፡

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን
Ethiopian Cooperative Commission
(ECC)

ከኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ጋር በመተባበር
በየሳምንቱ የሚታተም

# የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የዲጂታል ቴክኖሎጂ ተጠቃሚነት

**በዳኛቸው ቀደማቸው**

ኢትዮጵያ ዘመናዊ የፋይናንስ ቴክኖሎዎችን በመጠቀም ቀልጣፋና ውጤታማ አሠራሮችን ተግባራዊ ለማድረግ ዓልማ እየሠራች ትገኛለች። የፋይናንስ ኅብረት ሥራ ማህበራት የዘመናዊ ኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ሶፍትዌር ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ እንዲሆኑ እየተሠራ መሆኑን የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ፋይናንስ ልማት መሪ ስራ አስፈጻሚ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

በመሆኑም ኅብረት ሥራ ማህበራት ያላቸውን የፋይናንስ ዘርፍ ለማጠናከርና የቢዝነስ ሥራቸውን ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሳደግ የአይ ሲቲ ቴክኖሎጂ ዘርፍን ማሳደግ አስፈልጓቸዋል። ማኅበራቱ የአባላትን ፍላጎት የሚያሟላ እና ተወዳዳሪ የሆነ የዲጅታል ፋይናንስ አገልግሎትን አቅም ለመገንባት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ትኩረት ሰጥተው እየሠሩ ይገኛሉ።

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ለገጠሩ የሕብረተሰብ ክፍል የተሻለ የፋይናንስ አቅርቦት እንዲፈጠር ከአነስተኛ የገጠር ፋይናንስ ማስፋፊያ ተቋማት ፕሮግራም (RUFIP) በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ለገንዘብ ቁጠባና ብድር የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዮኖችን የዘመናዊ መረጃ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የመሠረተ ልማት ዝርጋታ ቴክኖሎጂ (Management Information System Software (MIS) በአብዛኞቹ ተቋማት ዘርግቷል። የዘመነ የፋይናንስ አገልግሎት ለአባሎቻቸው እንዲያቀርቡና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የአቅም ግንባታ ስልጠና እየተሰጠ ይገኛል።

በቴክኖሎጂ የታገዘ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒየን የፋይናንስ ሪፎርም አገልግሎት መስጠት የአባላትን ፍላጎት ለማርካት፣ የባለቤትነት ስሜት ለማሳደግ፣ ፍትሀዊ ተጠቃሚነትን ለማስፈን እና በዘርፉ እንቅስቃሴ ከፍተኛ ለውጥ ለማምጣት ጥቅም አለው። የፋይናንስ ሶፍትዌር መሠረተ ልማት ግንባታ ከዘርፉ አልሚ ፕሮጀክቶች ሁለት ጉዳዮችን ማለትም የጋራ መሠረተ ልማት መሣሪያዎችን መጠቀምንና የምርምር ሥራዎችን በተከታታይነት/በቀጣይነት የመደገፍ አስተሳሰብን አስተሳሰሮ ስር ነቀል ለውጥ ማምጣት የሚያስችል ነው።

የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት መሠረተ ልማትን በዚህ መልኩ ለማየት የአስተሳሰብና አመለካከት ለውጥ ሊኖር ይገባል። በመሆኑም የቴክሎጂ አጠቃቀም የጋራ ዕይታ፣ ከግልጽነት ወደ ተጨባጭ ተግባር፣ ከሚታሰብ በተግባር የሚታይ፣ ከአጭር ጊዜ ወደ ረጅም ጊዜ ተጠቃሚነት ከመሠረተ ልማት የተናጠል ዕይታ ወደ መሠረተ ልማት ግንኙነት ላይ ትኩረት የሚሸጋገር ሊሆን ይገባል። የዘመነ ኢንፎርሜሽን መሠረተ ልማት ማለት የሚጋሩት፣ የሚያድግ፣ ሊገለጽ የሚችል ስታንደርዳይዝድ፣ ቅይጥ (heterogamous)፣ ሰዎች የሚያቀነባብሩት፣ ቅደመ ተከተል ያለው፣ መሣሪያ፣ ፋሲሊቲ፣ ቴክኖሎጂ ሆኖ መረጃን የመፍጠር፣ የመጠቀም፣ የማከማቸትና የሥርፀት ድርጊት የሚፈጸምበት ሥርዐት ነው።

ኢንፎርሜሽን መሠረተ ልማት የአንድ ድርጅት ቴክኒካል መዋቅር የኔትወርክ ሥርዓት ነው። ኢንፎርሜሽን መሠረተ ልማት 8 መለኪያዎች (dimensions) አሉት። እነዚህም አካታችነት፣ ግልጽነት፣ ተደራሽነት፣ አስተማሪነት፣ ከተግባር ጋር የተሳሰረ፣ ስታንደርዳዊ የሆነ፣ መሠረት ኖሮት የተገነባና ሊጠገን /ሊስተካከል/ የሚችል የሚሉት ይጠቀሳሉ።

የዘርፉ የፋይናንስ መሠረተ ልማት ጽንሰ ሃሳብ ከኢንፎርሜሽን መሠረተ ልማት ጥናት፣ አደረጃጀትና ከሪፎርም አወቃቀር ጋር አስተሳስሮ ማየት ያስፈልጋል። መሠረተ ልማት ማህበራዊና ድርጅታዊ (organizational) ስፋትን መሠረት በማድረግ የሰው ልጅ የቴክኖሎጂ




ተጠቃሚነትን፣ ብሎም የማህበራትና የቴክኖሎጂ ዘርፎችን፣ ሥርዓቶችን በዳታ ልውውጥ፣ በሲስተም ተናባቢነት፣ በስታንዳርድ ተገቢነት፣ ጥገናና ዲዛይን ላይ ትስስር መኖሩን የሚያመለክት መሆን አለበት።

ፋይናንሺያል ዲጂታል መሠረተ ልማት ማለት ለአንድ ሀገር፣ ከተማ ወይም አካባቢ መረጃ በሰው ልጅ ተቀነባብሮ በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሠረታዊ አገልግሎት የሚሰጥበትና ለኢኮኖሚ ልማትና ዕድገት፣ ለሰው ልጅ ዘመናዊ አኗኗር የሚበሰርበት ነው። ዲጂታል መሠረተ ልማት ከሚባሉት መካከል ኢንተርኔት፣ ብሮድባንድ፣ ዋይፋይ፣ ዳታ ማዕከል፣ አፕሊኬሽኖች፣ አይ.ኦ.ቲ ወዘተ. ይጠቀሳሉ።

የማህበራቱ የገንዘብ ፍሰት መረጃ ተደራሽነትን በፍትሃዊነትና ዕኩልነት ለማዳረስ የሚታይ ክፍተት/ልዩነትን (Digital Divide) ማጥበብ ክልሎች ልዩ ትኩረት የሚያደርጉበት ተግባር ነው። ለመረጃ ክፍተት/ልዩነትን እንደ ተግዳሮት ከሚጠቀሱት የኢንተርኔት ተጠቃሚዎች ቁጥር፣ ኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂን የመጠቀም ጉዳይ በመንግሥት የተሰጠው ትኩረት፣ የተበታተነ አሰፋፈር፣ የዘርፉ ባለሙያዎች ዕጥረት፣ የግንዛቤ ፈጠራ ሥራ፣ የቴክኖሎጂ ክህሎት፣ ዕኩል ተጠቃሚነት፣ ቋንቋ፣ ሥርዐተ ፆታ፣ የትምህርት ደረጃ፣ ፍልሰት፣ የቦታ አቀማመጥ (Demography) ጥቂቶቹ ናቸው። በመሆኑም ተግዳሮቶችን ደረጃ በደረጃ በመፍታት የማህበረሰቡን የቴክኖሎጂ ተደራሽነት ማረጋገጥ፣ ያሉትንም መሠረተ ልማቶች በአግባቡ መጠቀምና ማህበረሰቡም እንዲጠቀም የማብቃት ሥራ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። ሲጠቃለል የፋይናንስ ቴክኖሎጂ መሠረተ ልማትን ማስፋፋት፣ ማደስና መጠቀም ለሰው ልጅ የገንዘብ ቁጠባና ብድር መረጃ ልውውጥ ማደግና መስፋፋት፣ የኑሮ ደረጃ መሻሻል መሠረታዊና የወቅቱ ትኩረት ሆኖ ይገኛል። የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት የዕድገትና የሥልጣኔ ደረጃ የሚለካው ቴክኖሎጂን በመጠቀምና ባለመጠቀም ወይም ለቴክኖሎጂ ትኩረት በመስጠትና ባለመስጠት ካላቸው ትኩረት እንደሆነ ብዙዎች ይስማሙበታል።

በመሆኑም አቅም በፈቀደው መጠን ቴክኖሎጂን ለመጠቀም፣ መሠረተ ልማትን ማስፋፋትና ደህንነታቸው እንዲጠበቅም አቅዶ መሥራት ያስፈልጋል። በሀገራችን ብሎም በክልላችን ያሉትን መሠረታዊ የመሠረተ ልማት አውታሮች መጠቀም የፋይናንስ መረጃ ልውውጥን እንደሚያፋጥን ማህበረሰቡን ማስገንዘብ፣ ተጠቃሚ ማድረግ፣ ራስን ማብቃት፣ የተጠቃሚ ቁጥርንም ማሳደግ፣ ከአላስፈላጊ አጠቃቀም ራስን ማቀብ፣ ለቴክኖሎጂ ማደግ ፈጠራን ማበረታታት፣ ግኝቶችን መለካት፣ ማስተዋወቅና ወደ ተግባር መቀየር ተገቢ ነው።

አድራሻ | የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን | 0115573448/ 0118592105 | ፖ.ሳ.ቁ. 19787 | Facebook: Ethiopia cooperative Commission | Website: www.fca.gov.et